5 የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት

ገፅ 3

የዞን 9 ጦማሪያን የዓለም ዐቀፍ ሽልማት አሸናፊ ሆኑ

ገፅ 3

“አብያተ ክርስቲያናቱን የንግድ ድርጅቶች ውጠዋቸዋል”
ዲያቆን ዳንኤል ክብረት

ገፅ 6



# የቀለም ቀንድ

ቅፅ 3 ቁጥር 9 መስከረም 7 2007 ዋጋ 10ብር

# ሕወሓትን ማጠናከር?



“የአቶ ሞላ አስገዶም ወደ ሕወሓት መመለስ፡ የሕወሓትን የመሰባሰብና እንደገና ለመጠናከር የመፈለግ ሁኔታ የሚጠቁም ነው”
አቶ ዳንኤል ተፈራ

ገፅ 4 እና 5

## ርዕሰ አንቀፅ

# ሁለቱ ዱርዬ ድርጅቶች እና የሁለቱ አገሮች ሕዝቦች መከራ

የኢትዮጵያ መንግሥት ሞላ አስገዶም በተባለ ግለሰብ የተመሩ የትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትሕዴን) አባላት ናቸው ያላቸው አካላት ከኤርትራ መንግሥት ታጣቂዎች ጋር ሁለቱ አገሮች በሚዋሰኑበት ድንበር አካባቢ ውጊያ በማድረግ ጳጉሜ 6 ቀን 2007 ዓ.ም. አመሻሹ ላይ ሱዳን ገብተው፣ መስከረም 2 ቀን 2008 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ መግለጹ ይታወሳል። አቶ ሞላ አስገዶም በበኩላቸው ከኢትዮጵያ ፈርስት ዶት ኮም ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ ‹‹የኤርትራ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመበታተን እንጅ ለአንድነቷ አይሠራም›› የሚለውን አቋም ገምግሞ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር መስማማቱን ገልጿል።

ሁሉም እንደሚያውቀው ሕወሓትና ሻዕቢያ እጅና ጓንት ሆነው የኖሩ ድርጅቶች ናቸው። ሕወሓትና ሻዕቢያ እየተጋገዙ የኢትዮጵያን ሠራዊት እንደወጉና ሁለቱ ቡድኖች ሥልጣን ከያዙ በኋላ ምን ያህል ያለ ይሉኝታ የኢትዮጵያን ሀብት ሲመዘብሩ እንደቆዩ ደግሞ የቀድሞውን የሕወሓት ታጋይ የአቶ ገብሩ አስራትን መጽሐፍ መመልከት ነው። ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በኋላ ነገሮች መልካቸውን ቀይረው አንዱ የአንዱ ጠላት መሆናቸውን ቢገልጹም አሁንም ያልተፈቱ ብዙ እንቆቅልሾች አሉ።

የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎችና እነአቶ ሞላ አስገዶም የሻዕቢያ መሰሪነትና አተራማሽነት እንደተገለጸላቸው ሲነግሩን የማይገባንና ትርጉም የማይሰጠን የዚህን አጥፊ ድርጅት ተግባር ገና ከጠዋቱ ከጥንቱ ስለምናውቀው ነው። ግራ ከገባቸውና ከታሪካ ከማይማሩ (ዴስፐሬት ከሆኑ) አንዳንድ ወገኖች በስተቀር ብዙኃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሻዕቢያን አጥፊ ባህሪ አሳምሮ ያውቀዋል። ሕዝቡ ከአርባ ዓመት በፊት የሚያውቀው እውነት ነው እንደአዲስ ግኝትና መገለጥ አምሮና ተቀባብቶ ሲነገር የምንሰማው። ሕወሓት በትጥቅ ትግሉ ወቅት ሻዕቢያ እንዳይሸነፍ ሽንጡን ገትሮ እንደታገለ፣ አገራችን የባህር በር ያሳጣትን ውሳኔ ከዚኸው አጥፊ ድርጅት ጋር እንደወሰነ፣ እያሌ ኢትዮጵያውያን በሁለቱ ድርጅቶች ውሳኔና ትብብር እንደሞቱ፣ ከቤት ንብረታቸው እንደተፈናቀሉ፣ እንደታሰሩ፣ አሁንም ቢሆን ‹‹የባህር በርን ጉዳይ አታንሱ፤ ከጠየቃችሁ ቀድመን የምንወጋችሁ እኛ ነን›› እንደሚባል ኢትዮጵያውያን አሳምረው ያውቃሉ። ለዚህ ነው ያን ሁሉ ግፍ አብረው ከፈጸሙ በኋላ ሻዕቢያን በአጥፊነት፣ እነሱን በአገር ጠባቂነትና ሰላም ወዳድነት ሲሾሙ ትዝብት ላይ የሚወድቁት። ሻዕቢያ ከትናንት እስከ ዛሬ ቀጠናውን ለማተራመስ ይሠራል። ይህን አሳምረን እናውቃለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለሻዕቢያ አተራማሽነት ከሕወሓት ምስክርነት የሚፈልግ አይመስለንም። ማን ከዚህ መሰሪ ድርጅት ጋር እንደሚተቃቀፍም ጠንቅቆ ያውቃል።

በመሠረቱ ሁለቱ ድርጅቶች በባህሪ አንድ ዓይነት ናቸው። ሕወሓት የሚዘውረው የኢትዮጵያ መንግሥትም እንደ ሻዕቢያ ጭር ሲል አይወድም። የሁለቱም ድርጅቶች የሥልጣን መሠረት የጦርነት ቀጠና መፍጠርና ሽብር መንዛት ነው። ሰላም የለሹ የአፍሪካ ቀንድ ለሁለቱ ድርጀቶች በእጅጉ ተመችቷቸዋል። ሁልጊዜም ሰላም ሲሆን ይባንናሉ፤ ሰላም አይፈልጉም። የአፈና አገዛዛቸውን ውጥረት በማንገስና ሽብር በመንዛት ለማስቀጠል በከፍተኛ ደረጃ ይሠራሉ። ሻዕቢያ ሁልጊዜም መከረኛውን የኤርትራ ሕዝብ ‹‹በሕወሓት የምትመራው ኢትዮጵያ ልትወረን ነው፤ የኢትዮጵያ የወረራ ስጋት እስካልቆመ ድረስ ሕገ መንግሥትና የመደበለ ፓርቲ ሥርዓት ብሎ ነገር የለም፣ ነጻ ሚዲያ አይታሰብም ወዘተ.›› እያለ እንደሚቀጠቅጠው ይታወቃል። እንደሚታየው በሻዕቢያ የአፈና አገዛዝ የተማረረው አብዛኛው የኤርትራ ወጣት በርሃና ውቂያኖስ ይብላኝ ብሎ አገሩን ጥሎ በመሰደድ ላይ ነው።

ሻዕቢያ ‹‹በሕወሓት የሚመራው የኢትዮጵያ መንግሥት ሊወረኝ ነው›› ሲል ሕወሓት/ኢሕአዴግ በበኩሉ ‹‹ሻዕቢያ ኢትዮጵያን ለማተራመስ እየሠራ ነው›› ይለናል። ብዙ ኢትዮጵያውያን በሻዕቢያ ድጋፍ የትጥቅ ትግል ያደርጋሉ በሚባሉት ድርጅቶች አባልነት እየተወነጀሉ ዘብጥያ እንደወረዱ ይታወቃል። ለኢሕአዴግ የአገር ቤቱን ተቃውሞ ለማኮላሸት የሻዕቢያ መኖር ጠቃሚ ነው። የኢሕአዴግ መኖርም የሻዕቢያ የህልውና መሠረት ነው። ለዚህ ነው አፋዊ በሆነ ሁኔታ አንዱ አንዱን በጠላትነት ይፈርጀው እንጅ ጨርሶ እንዲዳከምና እንዲሞት የማይፈልገው።

## ትዝብት

# ሕግ እንደ አገዛዝ መሣሪያ

በሪሁን አዳነ


ቀዝቃዛው ጦርነት በምዕራባውያን የበላይነት በተደመደመ ማግስት ወደ ሥልጣን የመጡት አፋኝ ድርጅቶች በዓለም ዐቀፍ ደረጃ በተከሰተው የኃይል አሰላላፍ ለውጥ አስገዳጅነት የመድበለ ፓርቲ ሥርዓትን ‹‹ለመቀበል›› ተገድደዋል። እነኝህ ዘመነኛ አፋኝ ደርጅቶች እንደ ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች ሁሉ ልዩ ልዩ ሥርዓታትን (ኢንስቲቲውሽንስ) ይዘረጋሉ። የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት፣ በነጻነት የመጻፍ፣ የመደራጀት ወዘተ. መብቶችን እና የዳኝነት ነጻነትን የሚቀበል ሕገ መንግሥት እንዲጸድቅ ያደርጋሉ። ልዩ ልዩ ዐዋጆችና ደንቦች እንዲወጡም ይደረጋል። እንደ የሰብአዊ መብቶች ተንከባካቢና የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ያሉ ተቋማትም ይቋቋማሉ። ይሁን እንጅ በአፈና ሥርዓት ውስጥ እነኝህ ሥርዓታት ከአገዛዝ መሣሪያነት የዘለለ ሚና የላቸውም። አፋኝ ድርጅቶች ከማንም በላይ የዳኝነት ነጻነት ተቆርቋሪዎች ለመምሰል ቢሞክሩም ሕግን በአገዛዝ መሣሪያነት በመጠቀም የሚስንቃቸው የለም። ግፈኛ አገዛዛቸውን በሕግ መሣሪያነት ይጠብቁታል። ሕግ ጠቅሰው የፈለጉትን ያስራሉ፤ ያሰቃያሉ። ፍጹማዊ የበላይነት በያዙበት ፓርላማ ያለማንም ከልካይ አሳሪ ሕጎችን ያወጣሉ። የሕጉ ኢ-ፍትሐዊነት የማይበቃ ይመስል የፍርድ ሂደቱንም በትዕዛዝ ያስፈጽሙታል።

ኢትዮጵያውያን በዚህ በኩል ብዙ ዓይተናል። የኢትዮጵያ የፍትሕ ሥርዓት ገብዓተ-መሬት የተፈጸመው በዚህ ኢሕአዴግ በሚመራው አገዛዝ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። በዚህች አገር ከኢሕአዴግ በፊትም ቢሆን ብዙ ሰዎች ሰብአዊ ክብራቸው ተገፎ ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ተበድለዋል፤ ታስረዋል፤ ተገድለውማል.። ሕግን መሣሪያ አድርጎ ዜጎችን መበደል፤ ማሰርና ማሰቃየት የዘወትር ተግባር የሆነው ግን በዚህ በዘመነ ኢሕአዴግ ነው። ማንም ሰው እንደሚገነዘበው፤ ዛሬ በአገራችን ሕግ የአገዛዙ መሣሪያ ነው። ሕግ የመኮርኮሚያ መሣሪያ ሆኗልና አገዛዙ ያልፈለገው ፖለቲከኛ ሕግ ተጠቅሶበት ይፈረድበታል። አገዛዙ ያልፈለገው ጋዜጠኛም ከዚህ አያመልጥም። የሥርዓቱ መሪዎችና መገናኛ ብዙኃኑ በአንድ ወቅት ‹‹ትልቅ ሰው ነው፤ ልማታዊ ባለሀብት ነው›› ሲሉት የከረሙት ባለሀብት አያስፈልግም በተባለ ማግስት ወንጀለኛ ተብሎ ‹‹ቫት ያጭበረበረ፣ የውጭ ምንዛሪ የደበቀ ወዘተ.›› ተብሎ ዘብጥያ ሲወረወር ታዝበናል።

በዘመነ ኢሕአዴግ ሕግ የአገዛዝ መሣሪያ እንጂ ዜጎች የሚገለገሉበት ወይም የሚዳኙበት አልሆነም። ዛሬ በዚህች አገር ‹‹ሕግ ነጻ ያወጣኛል›› የሚል ዜጋ አለ ለማለት ያስቸግራል። የፍትሕ ሥርዓቱን መጠበቅ፣ መንከባከብና ለሕግ የበላይነት ጥብቅና መቆም ያለባቸው ወገኖች ሁሉ ተሽመድምደዋል። የፍትሕ አካላቱ የሚሠሩት በባለሥልጣናት ትዕዛዝ መሠረት ነው። ባለሥልጣናቱ ለአቃቢያነ ሕጉና ለዳኞች ትዕዛዝ እንደሚሰጡ እየታወቀ፣ ‹‹በፍርድ ቤት ጉዳይ አንገባም፤ ፍርድ ቤት የያዘው ጉዳይ ነው ወዘተ.›› ሲሉ ይደመጣሉ። ነገርዬው የሌባ ዐይነ ደረቅ እንደሚሉት ዓይነት ነው።

ኢሕአዴግ ሕግና ሥርዓት የማይገስጸው የአፈና አገዛዝ ተክሏልና ሲፈልግ በገፍ ያለምክንያት ያስራል። ሲፈልግም እንዲሁ ያለምክንያትና ያለሥነ-ሥርዓት ይፈታል። ዜጎች ለምን እንደታሰሩ ሳይገለጽላቸው ይለቀቃሉ። ነገ ተመልሰው እንደማይታፈኑ ምንም ዓይነት ዋስትና የላቸውም። በቅርቡ የተወሰኑ ጋዜጠኞችና ሁለት የዞን ዘጠኝ ጦማሪያን ሲፈቱ ጓደኞቻቸው ተለይተው ቀርተዋል። የተፈቱት ለምን እንደተፈቱ አይታወቅም። ያልተፈቱትም ለምን እንዳልተፈቱ የሚታወቅ ነገር የለም። እነሀብታሙ አያሌው ፍርድ ቤቱ በነጻ ካሰናበታቸው በኋላ አሁንም አልተፈቱም። ለምን? የሚታወቅ ነገር የለም። በዚህ ኢ-ፍትሓዊና ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ተጠያቂ የሚሆን አካልም የለም። ከሰሞኑ ደግሞ የተወሰኑ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ተለቀዋል። የተለቀቁት ለምን እንደተለቀቁና የቀሩት ለምን እንዳልተፈቱ የሚታወቅ አጥጋቢ ምክንያት የለም። እውነትም ሕገ አራዊት!

በዲኦንሒር ፐብሊሺንግ ሚዲያ እና ኮምኒኬሽን ኃ.የተ.የግ. ማኅበር እየተዘጋጀ የሚቀርብ ሳምንታዊ ጋዜጣ



**ሥራ አስኪያጅ**
አበበ ውቤ
abekknewspaper@gmail.com

**ዋና አዘጋጅ**
ሙሉቀን ተስፋው
0910159783
mulukentesafaw@gmail.com
የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 09/297

**ሪፖርተር**
ትሑት ጥላሁን

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ነበዩ አድቨርታይዚንግ
0911 180933

**አታሚ**
ናታን ማተሚያ ቤት
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 1062

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 08
ቤ/ቁጥር 471
ስልክ፡0919396240

# ዜናዎች

## የዞን 9 ጦማሪያን የዓለም ዐቀፍ ሽልማት አሸናፊ ሆኑ

የዞን 9 ጦማርያን በዓለም ዐቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢ ድርጅት (ሲፒጄ) የሚዘጋጀው ሽልማት የዓመቱ አሸናፊዎች መሆናቸው ተገለጸ። ሲፒጄ በድረ ገጹ እንዳስታወቀው የሽልማቱ አሸናፊ የሆኑት ጦማርያን አቤል ዋበላ፣ አጥናፍ ብርሃኔ፣ ማህሌት ፈንታሁን፣ ናትናኤል ፈለቀ፣ ዘላለም ክብረት፣ በፈቃዱ ኃይሉ፣ ሶልያና ሽመልስ፣ እንዳልክ ጫላና ጆማኔክስ ካሳዬ ናቸው። ‹‹ለነጻው ፕሬስ እጅግ አስቸጋሪና ፈታኝ በሆነ ከባቢ ውስጥ የመንግሥትን አፈና ተቋቁመው ላበረከቱት አስተዋጽኦ እውቅናው ተሰጥቷቸዋል›› ሲል የገለጠው ድርጅቱ ኢትዮጵያ በ2007 ዓ.ም. ስድስት ጋዜጠኞችንና ጦማሪያንን ብትፈታም አሁንም ከደርዘን በላይ ጋዜጠኞች በእስር ላይ እንደሚገኙና አገሪቱ ለጋዜጠኞች አስቸጋሪ ከሆኑ ሦስት አገሮች ወስጥ አንዷ መሆኗን አስታውሷል።

የሽልማቱ አሸናፊ ከሆኑት ጦማሪያን መካከል በፈቃዱ ኃይሉ፣ አቤል ዋበላና አጥናፍ ብርሃኔ አሁንም በእስር ላይ የሚገኙ ሲሆን ዘላለም ክበረትና ማህሌት ፈንታሁን ከአንድ ዓመት በላይ ከታሰሩ በኋላ ሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም. ክሳቸው ተቋርጦ ከእስር ተለቀዋል። ሶሊያና ሽመልስ፣ እንዳልክ ጫላናና ጆማኔክስ ካሳዬ ደግሞ በስደት ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል።

## 5 የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ተፈቱ

### ‹‹በምን መስፈርት እኛን ብቻ መርጠው እንደፈቱን የምናውቀው ነገር የለም›› አቶ ያሲን ኑር

ከሦስት እስከ ሀያ ሁለት ዓመት የሚደርስ የእስር ቅጣት ከተፈረደባቸው የሙስሊሙ ማኅበረሰብ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት መካከል አምስቱ በሳምንቱ መጀመሪያ በምህረት ተለቀቁ። ሁሴን ኑሩ፣ አቡበከር አለሙ፣ ከቢር ይርጉ፣ ሙኒር ሁሴንና ባህሩ ዑመር አዲሱን የ2008 ዓ.ም. የዘመን መለወጫ በዓል ምክንያት በማድረግ ከተለቀቁት ዜጎች ጋር አብረው ከመውጣታቸው በስተቀር መንግሥት ከሌሎች ጓዶቻቸው ነጥሎ እነሱን ለምን እንደፈታቸው የሚያውቁት ነገር አለመኖሩን ተናግረዋል። ‹‹መንግሥት በሃይማኖታችን ላይ ጣልቃ አይግባ፤ መጅሊሱ በሕዝበ ሙስሊሙ የተመረጠ መሆን አለበት፤ የአህባሽ የግዴት አስተምህሮት ይቁም›› ወዘተ. በማለት ሲሟገቱ የቆዩት ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በተለይ ከ2003 ዓ.ም ወዲህ መንግሥት ጥያቄያቸውን በኃይል ለመመለስ በመሞከሩ ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያሰሙ ቆይተዋል። በአገር ዐቀፍ ደረጃ የተቀጣጠለውን የሕዝበ ሙስሊሙን ተቃውሞ ተከትሎ ብዙዎች የታሰሩ ሲሆን በአዲስ ዓመት ዋዜማ ከተለቀቁት አምስት የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ውጪ አሁንም ብዙ ዜጎች በእስር ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል።

በ2003 ዓ.ም. ከአወሊያ ትምህርት ቤት ሃያ ሦስት መምህራን ከሥራ ገበታቸው መባረራቸውን ተከትሎ የተማሪዎች ተቃውሞ እየበረታ ሲሄድ በመላ አገሪቱ በሺህዎች የሚቆጠር ፊርማ ተሰባስቦ የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ ተቋቁሞ ከመንግሥት ጋር ድርድር ተጀመረ። በጊዜው ከተመረጡ የኮሚቴ አባላት ውስጥ ያሲን ኑሩ፣ አቡበከር አህመድ፣ አህመዲን ጀበል፣ አህመድ ሙስጠፋ፣ ከሚል ሸምሱና ሌሎችም ይገኙበታል።

በ2004 ዓ.ም. በሮመዳን ጾም መግቢያ አካባቢ የተዘጋጀው የሰደቃና አንድነት መርሐ ግብር ‹‹የአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ አዲስ አበባ ውስጥ ስለሚካሄድ መርሐ ግብሩን ማካሄድ አትችሉም›› በሚል ምክንያት በመንግሥት ተከለከለ። ቀጥሎም ከመንግሥት ጋር ድርድር ላይ የነበሩት የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴዎች ታሰሩ። ለሁለተኛ ጊዜ የተመረጡ የኮሚቴ አባላት ጥረት ቢያደርጉም እነሱም ብዙ ሳይቆዩ እንዲሁ የታሰሩ ሲሆን ለሦስተኛ ጊዜ የተመረጡት አባላት ደግሞ አገር ጥለው ተሰደዋል። ‹‹ድምጻችን ይሰማ!›› የሚለውን የማኅበራዊ ሚዲያ ትግል የጀመሩትም እነርሱ እንደሆኑ ይታመናል። ድምጻችን ይሰማ የሚለው እንቅስቃሴ በርካታ የበይነ መረብ ዘመቻዎችን በማካሄድ የሙስሊሙን እንቅስቃሴ የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ ሲመራ ቆይቷል።

የታሰሩ የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት በ2007 ዓ.ም. የክረምት ወቅት እያንዳንዳቸው ከ3 እስከ 22 ዓመት የሚደርስ የእስር ቅጣት እንደተላለፈባቸው የሚታወስ ሲሆን ከእነኝህ ውስጥ አምስቱ የ2008 ዓ.ም. የዘመን መለወጫ በዓልን ምክንያት በማድረግ ከማረሚያ ቤት ተለቀዋል። ከተለቀቁት የኮሚቴ አባላት መካከል ያሲን ኑሩ በቤታቸው ተገኝተን ስናነጋግራቸው ‹‹በምን መስፈርት እኛ ብቻ ተመርጠን እንደተፈታን አላወቅንም። በየዓመቱ በይቅርታ የሚፈቱ ሰዎች እንዳሉ ብንገነዘብም ከታሰርነው መካከል በምን መስፈርት እኛን ብቻ ለይተው እንደፈቱን ግን የምናውቀው ነገር የለም›› በማለት ገልጸውልናል።

### በደቡብ አፍሪካ

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ ሊነጠቅ መሆኑ ተጠቆመ




በደቡብ አፍሪቃ አገረ ስብከት ዋና ሥራ አስኪያጅ እና በጆሐንስበርግ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ በሆኑት ቆሞስ አባ ጥዑመ ልሳን አዳነ ሕገ ወጥነት የተነሣ በደቡብ አፍሪቃ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያን ዕውቅና ሊነጠቅ መሆኑ ተጠቆመ።

‹‹ሰሚ ያጣ ጩኸት›› በሚል ርእስ ከደቡብ አፍሪካ የደረሰን ዘገባ እንደሚያትተው በመላው ደቡብ አፍሪቃ ያለችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ በደቡብ አፍሪቃ መንግሥት አትራፊ ባልኾኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች ዐዋጅ ሕግ መሠረት እ.ኤ.አ. በ26/01/1999 ሕጋዊ ፈቃድ አግኝታ፣ በቁጥር 006-083 መሠረት የተፈቀደላት እና የተመዘገበ ሕጋዊ ሰውነት ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት።

ይህ ሲኾን ታድያ፣ ቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ የሒሳብ ሪፖርቷን ለደቡብ አፍሪቃ የገቢዎች ቦርድ ማሳወቅ ይኖርባታል። ይኹንና ላለፉት ስምንት ዓመታት ምንም ዐይነት የሒሳብ ሪፖርት አልቀረበም። ስለ ጉዳዩ የሚመለከተው አካል በተደጋጋሚ ሲጠይቅ ቢቆይም አንዳችም ምላሽ ባለማግኘቱ፣ ፈቃዳችን ተሰርዞ ቤተ ክርስቲያናችን እንዳትዘጋ ከፍተኛ ስጋት ላይ ወድቀናል ሲሉ የሚያትቱት ወገኖች አክለውም ይህን ስጋታችንንና ሌሎች መሠረታዊ ችግሮቻችን፣ ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት እና ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ልዩ ጽሕፈት ቤት አቅርበን ነበር። ቅዱስ ሲኖዶስም የጉዳዩን አሳሳቢነት አምኖበት በጥቅምቱ የምልአተ ጉባኤ ስብሰባ ከተነጋገረበት በኋላ፣ የሒሳብ ሪፖርቱ በአስቸኳይ ተሠርቶ ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ፤ በውጭ ኦዲተርም እንዲመረመር ትእዛዝ ሰጥቶ ነበር። ይኹንና ትዕዛዙ ከተላለፈም በኋላ ሒሳቡ ተሠርቶ፣ ሪፖርቱ ባለመቅረቡ ውሳኔው ተፈጻሚ መኾን አልቻለም፤ የውጭ ኦዲቱም አልተከናወነም በማለት ምሬታቸውን ይገልጻሉ። ምደባቸው፣ ከአገሪቱ መንግሥት ሕግ እና ከሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን አንጻር ጥያቄ ተየነሳባቸው እና ‹‹ረዳት ጳጳስ ነኝ›› የሚሉት ሥራ አስኪያጁ፣ የቤተክርስቲያኒቱን ሕጋዊ ህልውና ለአደጋ አጋልጠውታል ተብሏል።

## የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ነገ በይፋ ሥራ ይጀምራል


በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከተያዙት ፕሮጀክቶች አንዱ የሆነው የአዲስ አበባ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት ግንባታው ተጠናቆ ከነገ መስከረም 9 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ አገልግሎት መስጠት እንደሚጀምር ተጠቆመ። ከታቀደው ከአንድ ዓመት በላይ እንደዘገየ የተገለጠው የቀላል ባቡር አገልግሎቱ የከተማዋን የትራንስፖርት ችግር በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል። የባቡር ትራንስፖርቱና የመኪኖች እንቅስቃሴ መስተጋብር አሁንም በበቂ ያልተሠራበት እንደመሆኑ መጠን ብዙ ዜጎች የአደጋ ሰለባ ሊሆኑ ይችላሉ የሚለው የብዙዎች ስጋት ነው።




## የደራሲ አበራ ለማ መጽሐፍ ይመረቃል

‹‹ቅንጣት - የኔዎቹ ኖብሌቶች›› በሚል ርእስ በአግዮስ ኅትመትና ጠቅላላ ንግድ ሥራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አሳታሚነት የታተመው የአንጋፋው ደራሲ አበራ ለማ መጽሐፍ ዛሬ መስከረም 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ከቀኑ 8፡00 እስከ 10፡30 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ አዳራሽ እንደሚመረቅ ታውቋል። በዕለቱ ሐያሲ አብደለ ዕዝራ በመጽሐፉ ላይ ዳሰሳዊ ግምገማ እንደሚያቀርቡ የተገለጠ ሲሆን ወይይት እንደሚደረግም ከመርሐ ግብሩ አዘጋጆች ያገኘነው መረጃ ያስረዳል።

# ሕወሓትን ማጠናከር?



**መንግሥት ሞላ አስገዶም በተባለ ግለሰብ የተመሩ የትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትሕዴን) አባላት ናቸው ያላቸው አካላት ከኤርትራ መንግሥት ታጣቂዎች ጋር ሁለቱ አገሮች በሚዋሰኑበት ድንበር አካባቢ ውጊያ በማድረግ ጳጉሜ 6 ቀን 2007 ዓ.ም. አመሻሹ ላይ ሱዳን ገብተው፣ መስከረም 2 ቀን 2008 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ መግለጹ ይታወሳል። የመንግሥትን መግለጫና የመንግሥት መገናኛ ብዙኃንን ተደጋጋሚ ዘገባ ተከትሎ ብዙ አስተያየቶች እየተሰጡ ነው። መንግሥትና የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ዜናው በከፍተኛ ደረጃ እንዲጮህ የፈለጉበት ምክንያትና የአቶ ሞላ መግለጫም ብዙ ጥያቄዎችን ማጫረቻው አልቀረም። የተወሰኑትን እንያቸው፡-**

## ጥያቄ 1

### እውን <<ትሕዴን>> የሚባል ድርጅት አለ?

ራሱን የትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትሕዴን) በማለት ስለሚጠራው ድርጅት ህልውና ብዙ ሲባል መቆየቱ የሚታወቅ ነው። አንዳንዶች ‹‹ድርጅቱ ቀደም ሲል የሕወሓት ታጋይ በነበሩና በኋላ ከሠራዊቱ በተቀነሱ አኩራፊዎች የተቋቋመ ድርጅት ነው›› ሲሉ ሌሎች ‹‹የድርጅቱ አባለት በ1993 ዓ.ም. በሕወሓት ወስጥ የተከሰተውን መከፋፈል ተከትሎ ትግሉን በሰላማዊ መንገድ መቀጠል ይሻላል ካሉት ውሱን ዜጎች ጋር በሐሳብ ልዩነት ምክንያት የትጥቅ ትግል የጀመሩ ናቸው›› ይሏቸዋል። ኤርትራዊው ምሁር ዶ/ር ተስፋጽዮን መድኃኔ በበኩላቸው ‹‹የትግራይ ትግርኝን አጀንዳ ለማስፈጸም ከኢትዮጵያ (ትግራይ) ወደ ኤርትራ የሄዱና ኤርትራ ወስጥ ኢሳያስ አፈውርቂንና የኢሳያስን የአፈና አገዛዝ በመጠበቅ ላይ ያሉ ቅልብ ኃይሎች ናቸው›› ይሏቸዋል። ድርጅቱ ‹‹መቼ፣ በነማን፣ ለምንና እንዴት ተመሠረተ›› የሚለው ነጥብ አከራካሪ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ይኸው ድርጅት በኢትዮጵያ ላይ ይህ ነው የሚባል ጥቃት ፈጽሞ እንደማያውቅ ይታወቃል።

በአብዛኛው የድርጅቱና የድርጅቱ መሪዎች ናቸው የሚባሉ ሰዎች ስም የሚሰማው እንደ አሜሪካ ድምጽ ባሉ በውጪው ዓለም በሚንቀሳቀሱ መገናኛ ብዙኃን አካባቢ ነው። ለዚህም ይመስላል ብዙ ወገኖች የሰሞኑ ዜና ሲነገር ግርታ የተፈጠረባቸው። የተባበሩት መንግሥታት በሚያወጣው ሪፖርት ስለዚህ ኃይል ይግለጽ እንጅ እንደተለመደው የተመድ ሪፖርት ውስብስብ የሆኑ ነጥቦችን አይዳስስም፤ ድርጅቱ ራሱ ስለራሱ ከሚገልጸው ውጪ ለምን፣ በማንና እንዴት ተመሠረተ የሚሉት አንኳር ጉዳዮች በጥልቀት አይዳሰሱም። ስለታጣቂ ድርጅቶች ጥልቀት ያለው ዘገባ የሚቀርበው ድርጅቶቹ በመንግሥት ላይ ጉዳት ሲያደርሱና ሰብአዊ ቀውስ ሲፈጠር ነው።

## ጥያቄ 2

### ትሕዴን የኢትዮጵያን መንግሥት በኃይል ለመገልበጥ ሊታገል ይችላልን?

‹‹እውን ትሕዴን የሚባለው ድርጅትና አባላቱ በሕወሓት የበላይነት የሚሽከረከረውን የኢትዮጵያን መንግሥት በኃይል ለመገርሰስ ሊታገሉ ይችላሉ ወይ?›› የሚል አስተያየት ይሰነዘራል። ሕወሓት ሠራዊቱን፣ የደህንነት ተቋሙንና እርሱን ተጠግቶ የከበረውን ደራሽ የከበርቴ ኃይል በመያዝ ላለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት የፖለቲካ የበላይነቱን አስጠብቆ እንደቆየ የሚታወቅ ነው። በመሆኑም የሕወሓት ፍፁም የበላይነት በሰፈነባት ኢትዮጵያ ውስጥ ይህን አገራዊ ሁኔታ የሕይወት መስዋዕትነት የሚጠይቅ ትግል አድርጉ አገዛዙን በኃይል ለመገርሰስ የሚታገል አካል ይኖራል ብሎ መናገር በእጅጉ ያስቸግራል። የድርጅቱ መሪ የሕወሓት ታጋይ የነበሩ ናቸው ሲባል ደግሞ ነገሩን ይበልጥ ያወሳስበዋል። እውነት የሕወሓት ታጋይ የነበሩና ከሠራዊቱ በመቀነሳቸው ያኮረፉ ናቸው ቢባል እንኳን እንደሌሎች ከሕወሓት ያፈነገጡና ከድርጅቱ የተሰናበቱ አባላት ንግዳቸውን እያጧጧፉ ከመቀመጥና የከበርቴ ሕይወት ከመምራት የሚያግዳቸው ነገር ይኖራል ተብሎ አይታሰብም። ብዙዎች ድምጻቸውን አጥፍተው እንደሚነግዱና አንዳንዶችም ትላልቅ መንግሥታዊና ቀጠናዊ ድርጅቶችን በመምራት ላይ እንደሚገኙ ይታወቃልና።

የድርጅቱ መሪ እንደሆኑ የተገለጸው አቶ ሞላ አስገዶም በአስመራ ቆይታቸው የኤርትራ መንግሥት በወር 25 ሺህ ናቅፋ ለቤት ኪራይ ይከፍልላቸው እንደነበርና አራት ተሽከርካሪዎችን ለመንቀሳቀሻ መድቦላቸው ምቹ ሕይወት ይኖሩ እንደነበር ተናግረዋል። የኤርትራ መንግሥት አቶ ሞላ የተመቻቸ ሕይወት እንዲኖሩ ማድረጉን ብንቀበል እንኳን ያቺ በችጋር የምትላጋና የዜጎቿ ሲኦል የሆነችው ኤርትራ እኚህ ግለሰብ የሚመሩትን ሠራዊት በቋሚነት የሚመግብ፣ የሚያስታጥቅና የሚያሰለጥን አቅም ሊኖራት እንደማይችል ግልጽ ነው። ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ድርጅቱ ብሔረሰባዊ ማንነትን መሠረት አድርጎ የተቋቋመ ነውና በቋሚነት ሊደግፉት የሚችሉት የብሔረሰቡ አባላት ናቸው። ይሁን እንጅ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የትግራይ ብሔረሰብ አባለት ሕወሓትን ይደግፋሉ፣ ሕወሓት ከተሳሳተ እንዲሻሻል ይመክራሉ እንጅ ሕወሓትን በኃይል የሚያስወግድ ድርጅት ይደግፋሉ ማለት የሚቻል አይደለም። የለየለት የፖለቲካ ደሃ ካልሆነ በስተቀር ማንም ይህን ይገነዘባል። እውነትም ታጋዮች ከነበሩ እነአቶ ሞላም ቆምንለት ለሚሉት ሕዝብ ከሕወሓት የተሻለ ነገር እንደማያመጡለት አሳምረው ያውቃሉ። ለዚህ ነው ‹‹እውን ይህ ድርጅት እንደተባለው ሕወሓት የሚዘውረውን መንግሥት በኃይል ለመገርሰስ ሲሠራ ነበር ወይ? ሕወሓት የሚዘውረውን መንግሥት ለመገልበጥ የሚያስችል ምክንያትስ አለው ወይ? እነ አቶ ሞላ ኤርትራ ወስጥ የቆዩት አንዳንዶች እንደሚሉት ኤርትራ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን ለማዳከም ነው ወይስ ሌላ የተለየ ተልዕኮ አላቸው?›› ብሎ መጠየቅ ተገቢ የሚሆነው።

## ጥያቄ 3

### ትሕዴን የሚባለውን ያህል ሠራዊት ሊኖረው ይችላልን?

አቶ ሞላ ከ800 በላይ ታጣቂዎችን አስከትለው እንደመጡ ተገልጿል። የድርጅቱ ምክትል ሊቀመንበር ነኝ ያሉ አቶ መኮንን ተስፋይ የሚባሉ ግለሰብ በበኩላቸው ለአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ በሰጡት አስተያየት ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ውሱን ሰዎች መሆናቸውን ተናግረዋል። የሁለቱን ግለሰቦች አስተያየት ወደጎን እንተወውና ‹‹እውን ድርጅቱ የሚባለውን ያህል ታጣቂ አለው ወይ? የሚባለወን ያህል ሠራዊት ካለውስ አባላቱ ከወዴት የተገኙ ናቸው? ለምን ዓላማ?›› በሚሉ ነጥቦች ላይ እናተኩር። እንደ ህልውናው ሁሉ የሠራዊቱ ብዛትም አከራካሪ ነው። በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን በአቶ ሞላ መሪነት ወደኢትዮጵያ የገቡ ናቸው ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ ሁሉም ከኤርትራ የተመለሱ ታጣቂዎች ሳይሆኑ ለፕሮፓጋንዳ የተጨማመሩ ሰዎች አሉ የሚባለውን ያህል ኤርትራ ውስጥ ቀሩ ከሚባሉት ውስጥም ብዙዎቹ የሻዕብያ ሠራዊት አባላት ናቸው የሚሉ አልታጡም። ይሁንና አከራካሪነቱ እንዳለ ሆኖ አምስትም መቶም ይሁን ስምንት መቶ ቀላል ኃይል አይደለም። ለመሆኑ ይህን ያህል ሰው ለምን ዓላማ ወደኤርትራ ሄዶ በርሃ ላይ በችግር እየኖረ የሕይወት መስዋዕትነት በሚያስከፍል ተግባር ላይ ለመሰማራት ቆረጠ? ይህ ሁሉ ሰው ከትግራይ ክልል ወደ ኤርትራ ሄዶ ከኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል ጋር ለመዋጋት የወሰነው ለትግራይ ክልል ከሕወሓት የተሻለ ምን ዓይነት ለውጥ ለማምጣት ነው? ብዙ ጥያቄዎችን የሚጋብዝ ነው።

ኢትዮጵያ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገበች ነው በሚባልበት በዚህ ዘመን ይህን ያህል ዜጋ የሕይወት መስዋዕትነት በሚያስከፍል ትግል ውስጥ መሄዱ በራሱ ሌላ ጥያቄ የሚያጭር ነው። ሥራ ፈጠራው፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ልማቱ፣ ተፈጥሯል የተባለው ሚሊዬነር አርሶ አደር የት ሄደ?

## ጥያቄ 4

### በታጣቂዎች መምጣት ማን ምን ያተርፋል?

በመንግሥት በኩል በአቶ ሞላ የተመራው ታጣቂ ኃይል ወደኢትዮጵያ መምጣቱ ለትሕዴን ታላቅ ውድቀት እንደሆነና ይኸው ኃይል የትጥቅ ትግሉን ትቶ የመጣው አባላቱ በአገሪቱ ልማት በመሳባቸው እንደሆነ ተገልጿል። ክስተቱ ለትሕዴን፣ የትጥቅ ትግል ለሚያካሂዱት ሌሎች ድርጅቶችና ለሻዕቢያም ትልቅ ኪሳራ ነውም ተብሏል። በመንግሥት በኩል የሚሰጠው አስተያየት እንዳለ ሆኖ የታጣቂውን ቡድን መምጣት ሕወሓትን ለማጠናከር የተያዘው ተግባር አንድ አካል እንደሆነ የሚገልጹ ወገኖችም አሉ። ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር ‹‹ሕወሓትን ገድለዋታል›› የሚሉ የሕወሓት አባላትና ደጋፊዎች ስለመኖራቸው ተደጋግሞ ተዘግቧል። አቶ መለስ ‹‹የሥልጣን መጀመሪያም መጨረሻም እኔ ነኝ›› በማለት ሁሉንም ነገር ጠቅልለውት በመቆየታቸውና አብዛኛው የትግራይ ወጣት በቢዝነስ ሥራ ላይ ስላተኮረ ሕወሓት ወጣትና ተስፋ የሚጣልበት የፖለቲካ መሪ ማፍራት አልቻለችም። በዚህ ምክንያት መተካካት የሚባለው ስትራቴጂ አንዱን ነባር ታጋይ በሌላ ነባር ታጋይ ከመቀያየር የሚያልፍ አልሆነም። ሕወሓትን የሚመሩት አሁንም በዚያው በትጥቅ ትግሉ ያለፉ ተጋዳላዮች ናቸው።

የሁሉም ነገር አልፋና ኦሜጋ ሆነው የቆዩት አቶ መለስ እንደሞቱ ‹‹ሕወሓትን እንታደግ›› በሚል ዘመቻ ከዚህ ቀደም ከድርጅቱ የተለዩትን ሰዎች የማግባባት እንቅስቃሴ እንደነበር ይታወቃል። እንደ አቶ ስየ ያሉት ብዙዎችም ወደድርጀቱ አይመለሱ እንጅ አፋቸውን ዘግተው ተቀምጠዋል። በኦፊሴል ባይደግፉም ከትችትና ከተቃውሞ ጋብ ማለታቸው በራሱ ትልቅ ድጋፍ እንደሚሆን ግልጽ ነው። አሁንም ግን የሕወሓት የአመራር ችግር አልተቀረፈም። አንዳንድ ምንጮች እንደሚሉት የእነአቶ ሞላ መምጣት ከዚህ የአመራር ክፍተት ጋር የተያያዘ ነው። ይህ እነአቶ ሞላ በሕወሓት ውስጥ የተፈጠረውን የተተኪ አመራር ክፍተት ይሞላሉ ወይም መሙላት ይችላሉ ማለት አይደለም። እንደ ምንጮች ገለጻ ይኸው ታጣቂ ኃይል ኤርትራም ሆኖ የሕወሓትን ሥራ ሲሠራ የቆየ ድርጅት በመሆኑ ግዳጁን ፈጽሞና የተወሰነውን ኃይሉን እዚያው ትቶ ወደኢትዮጵያ የመጣው በአንድ በኩል የሌሎችን ድርጅቶች ቅስም ለመስበር፣ በሕዝቡ መካከል ውዥብር ለመንዛትና የሕወሓትን አይበገሬነት ለማሳየት ሲሆን በሌላ በኩል የዲፕሎማሲ ድል ለማግኘት ሲባልም ጭምር የተወሰደ እርምጃ ነው። እዚያ የቀረው ኃይል በበኩሉ በአዲስ አመራርና በአዲስ ስልት የተለመደውን ተግባር ይቀጥላል። ጥረቱ ከውስጥም ከውጪም ሕወሓትን ለማጠናከር ነው። በዚህ አስቺጋሪና የሸፍጥ ፖለቲካ በሞላበት የአፍሪካ ቀንድ ቀጠና ውስጥ ብዙ ጉደኛ ነገሮች ይደረጋሉ፤ ብዙ ጉደኛ ድርጅቶች መኖራቸውም የታወቀ ነው።

# ወቅታዊ ቃለ-ምልልስ

## “የአቶ ሞላ አስገዶም ወደ ሕወሓት መመለስ፡ የሕወሓትን የመሰባሰብና እንደገና ለመጠናከር የመፈለግ ሁኔታ የሚጠቁም ነው”

### አቶ ዳንኤል ተፈራ

**የቀለም ቀንድ ባልደረቦች በአገራችን ወቅታዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ከአቶ ዳንኤል ተፈራ ጋር አጭር ቆይታ አድርገዋል። ወይይቱን እንሆ፡-**



የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዶክተር ያጣ በሽተኛ ነው

**የአገራችንን (ወቅታዊ) የፖለቲካ ሁኔታ እንዴት ትገመግመዋለህ?**

እንግዲህ ግምገማ ሲባል ወይም በገደምዳሜ የአገራችንን የፖለቲካ ሁኔታ ገምግሜዋለሁ ለማለት ጥናት ያስፈልጋል። ነገር ግን እንደ አንድ ግለሰብ የሚሰማህን ተናገር ከተባልኩ የአገራችን ፖለቲካ ላለፉት 50 ዓመታት በበሽታ የኖረ፣ ከበሽታዉ ያልተፈወሰና አሁንም እያሳለው ያለ ነው። በአጭሩ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዶክተር ያጣ በሽተኛ ነው። ለባለፉት 50 ዓመታት የተነሱት የለውጥ ጥያቄዎች ወይም የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ይከበር ጥያቄዎችን በጉልበት እየደፈጠጠ የሚያልፍ፤ ሐሳብ ያለው ሳይሆን ጉልበት ያለው የሚነግሥበት፤ ሐሳብ ያለው የሚደፈቅበት ዓይነት ነው። አለመታደል የሚሉት ዓይነት ነዉ።

ለባፉት 50 ዓመታት ስል ግርታ እንዳይፈጠር ካስፈለገ በአገራችን የለውጥ ጥያቄ በድፍረት ያነሱት ወንድማማቾች መንግሥቱ ንዋይና ግርማሜ ንዋይ ናቸው ብለን ብንነሳ ማለት ነው። የነዚህ ግለሰቦች ጥያቄ በአፄ ኃይለሥላሴ ሥርዓት ተጨፈለቀ። የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት መልስ ማነቂያ ገመድ ይዞ መምጣት ነበር፤ አነቋቸው። ነገር ግን ያነቁት የግለሰቦችን አንገት እንጂ ሐሳባቸውን ስላልነበር ጥያቄው ቀጠለ፤ ተማሪው አቀነቀነው። ረጅሙን ታሪክ ለማሳጠር የተማሪው ጉልበት የተሻለ የመሣሪያ ጉልበት ያለው ደርግ ነጠቀው።

የደርግ ክፋቱ መንጠቁ ብቻ አይደለም። የተነሳውን ጥያቄ ተገንዝቦ የለውጥ ኃይል አለመሆኑ ይመስለኛል። እናም በደርግ ላይ ያኮረፉ ኃይሎች ተነሱ። የጉልበት ብልጫ ሲያገኙ በተራቸዉ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ገቡ። ሕወሓት/ኢሕአዴግ ቤተ መንግሥት ሲገባ አሁንም ለውጥ ተጠበቀ። ለውጡ ግን ብቅ ሊል አልቻለም። ወጡ አልጣፈጠንም፤ ጉልቻ መቀያየር ብቻ ሆነ። ቴዲ አፍሮ እንዳለው አዲስ ንጉሥ እንጅ ለውጥ ሊመጣ አልቻለም። ስለዚህ በኔ የግል ግምገማ የአገራችን ፖለቲካ ቁሞ ቀር ነው። ባለበት የሚረግጥ፤ ለውጥ የሚፈራ፤ አዲስ ሐሳብ የማይወድና ጉልበተኛ። ይኸ ነው የኔ ቁንጽል ዕይታ።

**ስላለፈው የ2007 ዓ.ም. ምርጫ ከተለያየ አቅጣጫ ብዙ ተብሏል። አንተ በግልህ ሂደቱን እንዴት አየኸው?**

ፕ/ር መስፍን እንደሚሉት ያው የቁልቁለት ጉዞ ነው። ‹‹ከ99.6 በመቶ ወደ 100 በመቶ›› የኢሕአዴግን ሞኝነት ያጋለጠ ምርጫ ነው። እኔ በግሌ የኢሕአዴግ መገለጫ በመሆኑ ብዙ አልተከፋሁም። የእነርሱ ግልባጭ ወይም ፎቶ ኮፒ የሆኑ አይረቤ ተቃዋሚዎችን አሾልኮ በማስገባት ሲያላግጥ መክረም ይችል ነበር። አምስት ዓመቷን ጠብቀው ለኢሕአዴግ ከራቫት ካላሰርን፣ ጫማ ካልጠረግን የሚሉ ተቃዋሚዎችን ሁሉ ኩም ያደረገ ነው። ግን ምርጫ ሲባል በብስጭት ምርጫ አለ እንዴ? የሚሉ አሉ። እኔ በግሌ ለ2007 ዓ.ም. ምርጫ እውቅና ለመስጠት እቸገራለሁ። ኢሕአዴግ ይህን ምርጫ ‹‹ያሸነፈው›› አስቀድሞ ነው። መንገዱን የጠረገው አስቀድሞ ነው። ስለዚህ ከምርጫ ውጭ ወዳለህ ጥያቄ እንለፍ።

**ስለዚህ በቅርቡ መስከረም መጨረሻ ሥራውን ለሚጀምረው ፓርላማ ስሜት የለህም ማለት ነው?**

(ሳቅ) ያው ‹‹የኢሕአዴግ ምክር ቤት በፓርላማ›› በለው። በፓርላማው የክርክር ሕይወት የሚኖር አይመስለኝም። ከአንድ ሳሙና የወጣ ፋብሪካ ዓይነት ነው። በቅርጽም በይዘትም ተመሳሳይ ነው፤ ስለዚህ ምንም ነገር አይጠበቅም። በኢሕአዴግ ጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀው በምክር ቤቱ ይጸድቃል። ሕይወት ባለበት ይቀጥላል ማለት ነው።

**ስለተቃዋሚ ድርጅቶችስ ምን ትላለህ?**

እንግዲህ ተቃዋሚ ድርጅት ሲባል የትኞቹን ነው? በሰላማዊ ትግል የሚያምኑ ድርጅቶች አሉ። የሰላም ትግል አያዋጣም ብለው መሣሪያ ያነሱም አሉ። እኔ በቅርበት ስለማውቀው በሰላማዊ ትግል ስለሚያምኑ የአገሬ ተቃዋሚዎች ብናገር ይሻለኛል። ‹‹ሀገር የተቀማ ትውልድ›› በሚለዉ መጽሐፌ ‹‹የተቃውሞዉ ጎራ›› በሚል ለመዳሰስ ሞክሬያለሁ። የተቃውሞው ጎራ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ከሚፈጥረው ችግር፣ ጠልፎ መጣልና በፈለገው ጊዜ እንደ ፈንጅ በርቀት መቆጣጠሪያ የሚጠቀምባቸውን አስርጎ ከማስገባት በተጨማሪ ዘርፈ ብዙ ችግር ያለበት ነዉ። ዋነኛዉ ችግር ሁሉም ሊቀመንበር መባል መፈለጉ ነው። በአገራችን ራሱ ኢሕአዴግ የሚፈለፍላቸዉ ጫጩት ፓርቲዎች እንዳሉ ሆኖ ሊቀመንበር ለመባል ፓርቲ የሚያቋቁመው ብዙ ነው። ‹‹እኔ›› የሚለው ራስን አብዝቶ የመውደድ ቃልም ሌላ ችግር ነው። በተጨማሪም የፓርቲ ዲሲፕሊን አይከበርም። ስለዚህ እነዚህ ችግሮች ተደማምረው ‹‹ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል›› እንዲሉ ኢሕአዴግ ሳይጠራ እየገባ ያፈርሳል። በጣም በጣም ግዙፍ የተቃውሞ ጎራ ችግር ግን የኢሕአዴግ ኃላፊነት አለመሰማት ችግር ነው። ኢሕአዴግ ሥልጣኑን ለማቆየት እንደመንግሥት ከማሰብ ወጥቶ አደገኛ ቦዘኔ የሚሆንበት ጊዜ ብዙ ነው።

ምርጫ በመጣ ቁጥር ጋዜጠኞች፣ ፖለቲከኞችና አክቲቪስቶችን ማሰርና ማሳደድ የተለመደ ነው። ተደጋግሞ እንደታየው ደግሞ አንዳንዶቹ በእስር ላይ የቆዩ ዜጎች ከምርጫ በኋላ (አንዳንዶቹ የታሰሩበትና የተፈቱበት ምክንያት ሳይገለጥላቸው) ይለቀቃሉ፤ ይህ ሁኔታ በአገራችን የፍትሕ ሥርዓት ምን ይነግረናል?

አሁን ባለው የመንግሥት አወቃቀር ለስሙ ሕግ አውጭ፣ ሕግ ተርጓሚና ሕግ አስፈጻሚ የሚባሉ ግዙፍ አካላት አሉ። ስማቸዉ ብቻ ነው ግዙፍ እንጅ በተግባር የአንድ ፓርቲ ቋቶች ናቸው። በኢትዮጵያችን ዘለግ ያለ ጥያቄ ከሚነሳባቸዉ ተቋማት አንዱ የፍትሕ ተቋማችን ነው። ይህ ተቋም በደህንነት መሥሪያ ቤቱ መዳፍ ሥር ያለ በተለይ የፖለቲካ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ በሁለት እግሩ ቆሞ መበየን የማይችል ነው እየተባለ በተደጋጋሚ ይነገራል። ይህን እውነት የሚያረጋግጡ ሁኔታዎችን በቅርቡ ያየን ይመስለኛል። እነ ሀብታሙ አያሌው፣ ዳንኤል ሺበሽ፣ የሽዋስ አሰፋና አብርሐ ደስታን ፍርድ ቤቱ ‹‹ምንም መረጃ ስላልቀረበባቸው በነጻ አሰናብቻቸዋለሁ›› ቢልም የሚሰማው አላገኘም። ከዚህ በፊት የሰማያዊ ፓርቲና የቀድሞው አንድነት አባላት የነበሩ ግለሰቦች በፍርድ ቤት በነጻ ተሰናብተው አይለቀቁም ያለ አካል ነበር። ታዲያ ስለየትኛው ፍትሕ ነው ልንነጋገር የምንችለው? ድሮ አባቶቻችን ‹‹በሕግ አምላክ›› ይሉ ነበር። ዛሬ እኛ ልጆቻቸው ‹‹የፍትሕ ያለህ!›› እያልን ነው ያለነው። ‹‹ፍትሕ ፍትሕ...›› ሲባል ዘወትር እንሰማለን። ፍትሕ የሚሰጥ የፍትሕ ተቋም ተገንብቶ ቢሆን ኖሮ ‹‹ፍትሕ ፍትሕ..›› እየተባለ ሲጮህ አንሰማም ነበር። ምርጫ ሲቃረብ ዜጎች የሚታሰሩት ፍትሕ ስለሌለ ነው። በመጽሐፌ ላይ እንዳነሳሁት አገር ስለተቀማን ነው።

**በቅርቡ ሦስተኛ ሥራህ የሆነውን <<ሀገር የተቀማ ትውልድ>> የሚል መጽሐፍ ለንባብ አብቅተሃል። መጸሐፉን ለመጻፍ ያነሳሳህ ሐሳብ ምንድን ነዉ?**

እሺ! ያው ብዙ ሰዎች እንደሚሉኝ በዚህ መጽሐፍ አከራካሪ የሆኑ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ያነሳሳኝ ግን ከውስጤ ፈንቅሎ የሚወጣ የመገፋት ስሜት ነዉ። እውነቱን እንነጋገር ከተባለማ ይህች ትልቅ አገር የተወሰኑ ቡድኖች መፈንጫ ሆናለች። በመጽሐፉ ለማንሳት እንደሞከርኩት ‹‹አገር ማለት ሰው ነው፤ ተራራና ሸንተረሩ ብቻውን አገር አይሆኑም›› ይሉናል እንጅ አገር ማለት ኢሕአዴግ ሆኗል። እስኪ ተርታው ሰው እንኳ ምን እንደሚል ጠጋ ብለህ አዳምጥ፣ ‹‹ከኢሕአዴግ ጋር ጠጋ ብለህ አትበላም እንዴ?›› ነው የሚልህ። ሠርተህ ለመኖር፣ ለመብላትና ለመጠጣት ኢትዮጵያዊ ብቻ መሆን አልበቃ ብሏል። ጆርጅ ኦርዌል በድርሰቱ እንዳለው ሁሉ እኛም ‹‹ሁሉም ኢትዮጵያውያን እኩል ናቸው፤ የኢሕአዴግ አባላት የሆኑ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ከሁሉም የበለጠ እኩል ናቸው›› እንባለን። አገር መቀማት ማለት አገርህ በዜግነትህ ብቻ ልታገኝ የሚገባውን መሠረታዊ ነገር ስትነፈግ እንደማለት ነው። የዘመነ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያ እንደዚያ ናት።

በጠቀስከው መጽሐፌ ላይ ለመዳሰስ የሞከርኩት ይህንን ነዉ። ፖለቲካው ዋነኛ በመሆኑ በተቃዋሚ ጎራና በገዢው ግንባር በኩል ያለ ትውልድ አገር አልባነት ስሜት እንዲሰማው የሚተጉትን አካላት ለመዳሰስ ሞክሬያለሁ። ገና ብዙ ይጻፋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ታሪኩ ሳይደበዝዝ ‹‹አገር ይረከባል›› በሚባለው ትውልድ ላይ የተሠሩ ሸፍጦችን አነሳስቻለሁ። ግን በቂ ነው ብየ አላምንም። እንደ መነሻ ቀሚ፣ አስቀሚ፣ አቃሚና ተቀሚ ዋና ተዋናዮች ናቸው በመጽሐፌ።

**ታዲያ <<ያ ትውልድ>>ና <<ይህ ትውልድ>> መባባሉ አስፈላጊ ነውን?**

ጥሩ ጥያቄ ነው። ማንም ሰው የሚናገረው ስለሚያወቀው ነዉ። እኔ የዚህ ትውልድ አባል ነኝ። በዚህ ትውልድ ውስጥም አንዳንድ አስተዋጽኦዎችን ለማድረግ ሞክሬያለሁ። ስለዚህ እኔ የጻፍኩት ስለማውቀው ጉዳይ ብቻ ነዉ። እንደወጣት ለአገራችን ለሰላማዊው ትግል አስተዋጽኦ እናድርግ ስንል አልተቻለም። ይባሱንም አገር እንደሌለው መጻተኛ አሳደዱን። ስለዚህ እኔ ‹‹ያ ትውልድ ይህ ትውልድ›› እያልኩ ለመከፋፈል ሳይሆን የማውቀው ሐቅ የዚህ ትውልድ ስለሆነ ብቻ ነዉ።

**በመጽሐፍህ ላይ <<አንድነት>> የፈረሰው በፖለቲካ ውሳኔ እንደሆነ ጠቁመሃል። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ብዙ የአንድነት አባላት ከድርጅታዊ የፖለቲካ ትግል ውጭ መሆናቸው ግን ግልጽ ነው። ለመሆኑ ምን እየታሰበ ነው? ተስፋ ቆርጣችኋል ወይስ አዲስ ፓርቲ ለማቋቋም አስባችኋል?**

አንድነት ፓርቲ ላይ የተፈጸመው ታሪክ የማይረሳው ግፍና በደል ተስፋ ባያስቆርጥ ነበር የሚገርመኝ። አንድነት ላይ ታሪካዊ በደል እንደተፈጸመ ለማረጋገጥ ከፈለግክ ወደ ፓርቲው ጽሕፈት ቤት ጎራ በል። ምንም የለም ታፔላው ሳይቀር ተወስዶ ተሸጧል። የተፈለገውም ይኸው ነበር። መንግሥት የመሆን ቅርጽ የያዘውን አንድነትን አጥፍቶ ጉንዳኖችን መተካት። ያ ግቢው በአባላት የሚጨናነቅው አንድነት ወንበርና መጽሐፍ ለሚቸበችቡ ግለሰቦች ተሰጥቶ እንዲጠፋ ሲፈረድበት እንዴት አባላት ተስፋ አይቁረጡ? ስለዚህ ሌላ ፓርቲ ማቋቋም ጥቅሙ ምንድን ነው? ኢሕአዴግ ኃላፊነት የሚሰማው ስብስብ እስካልሆነ ድረስ ፓርቲ በስም እንጅ በተግባር በሚገዳደር መልኩ ማቋቋም አይችልም። እኔ በግሌ ፓርቲ ለማቋቋም ብየ የማጠፋው ሽራፊ ሰከንድ አይኖረኝም። ምክንያቴ ደግሞ በሰላማዊ ትግል ለመቀጠል በምንም በፓርቲ ፖለቲካ ተስፋ አይታየኝም። ሰላማዊ ትግሉን ሕዝቡ ራሱ ሊያካሂደው ይችላል። አንድነት በፈረሰበት መንገድ ምንም ዓይነት ፓርቲ ሊፈርስ ይችላል። ስለዚህ ፓርቲ ለማቋቋም መድከም ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ዓይነት ነገር ነው። ይህ የኔ የግል ዕይታ ነው። ትግሉን ለቀጠሉት ግን አክብሮቴ እንዳለ ነዉ።

**እስኪ በመጨረሻም ስለወቅታዊው የፖለቲካ ትኩሳት እናንሳ፤ በመጽሐፍህ ውስጥም <<የስየ አብርሃ ጠላት መለስ እንጅ ሕወሓት አይደለም>> የሚል ነገር ስለጠቀስክ ከዚኸው ጋር አያይዘህ የሞላ አስግዶምን ነገር እንዴት እንደተመለከትከው ግለጽልን?**

እኔ እንግዲህ የትጥቅ ትግሉ አካባቢ ብዙም እውቀት የለኝም። እንደው እንደ አንድ ዜጋ የሚሰማህን ንገረን ካልከኝ ጥልቅ የሆነ የፖለቲካ ትንታኔ የሚፈልግ ይመስለኛል። ይህ ከኤርትራ ተመለሰ የተባለው ግለሰብ ሲጀምርም የሕወሓት ታጋይ የነበረ ነው ይባላል። መረጃዎች እንደጠቆሙት የተቀናጀ ሠራዊት ከሆነ በኋላ ትጥቅ ትግል ጀመረ የሚል ነው።

የሆነው ሆኖ የሞላ አስግዶም መመለስ የሚጠቁመን ነገር ወይም የፖለቲካ ሁኔታ ያለ ይመስለኛል። እርሱም ሕወሓት ከመለስ ሞት በኋላ በሽኩቻ እየተዳከመ ነው የሄደው። ተተኪ አላፈሩም። ወጣቶቻቸው ፖለቲከኞች ሳይሆኑ ነጋዴዎች ናቸው። ስለዚህ የሕወሓት ጉዳይ ከነ አቶ ስብሐት ነጋ ጫንቃ መውረድ አልቻለም። በተጨባጭ እናንሳ ከተባለም ሕወሓት አኮረፉ ያላቸውን ኃይሎች መሰብሰብ ከጀመረ ትንሽ ቆየት ብሏል። አስቀድሞ ለገፉቸው ታጋዮች ጥሪ እያቀረበ ኃይል ለማጠናከር እየሞከረ ነው። ከሞላ አስግዶም ጋርም ተነጋግረዋል ከተባለ ይኸው ነው ሊሆን የሚችለው። ‹‹እንዴት ሕወሓት ስትሞት ዝም ብለህ ታያለህ›› ብለው የተደራደሩት ይመስለኛል። እና የአቶ ሞላ ወደ ሕወሓት መመለስ የሚጠቁመን ነገር ቢኖር የሕወሓትን የመሰባሰብና እንደገና ለመጠናከር የመፈለግ ሁኔታ ነው። በሌላ መልኩ ተተኪ ማጣታቸውንም የሚጠቁም ነው።

**የመጽሐፍህ ተቀባይነት እንዴት ነው?**

እስካሁን ጥሩ ነው። የመጀመሪያው ሕትመት አልቆ ወደ ሁለተኛ እየሄድን ነዉ። ይህ ማለት ሰው ፈልጎታል ማለት ነው። ዋናው ቁም ነገር ግን ተሸጠም አልተሸጠም የማውቀውን ሐቅ ማቅረቤ ላይ ነው።

# እንግዳ



# “አብያተ ክርስቲያናቱን የንግድ ድርጅቶች ውጠዋቸዋል”

**ዲያቆን ዳንኤል ክብረት**

**ሦስተኛው የበጎ ሰው ሽልማት ካለፉት ሁለት መርሐ ግብሮች ጋር ሲነጻጸር ምን ይመስላል?**

ብዙ ለውጦችና መሻሻሎች አሉ። አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ የደረሰው ቀስ በቀስ ነው። በመጀመሪያው መርሐ ግብር በአምስት የተለያዩ ዘርፎች እውቅና ተሰጥቷል። በሁለተኛው ዓመት ዘርፎቹ ወደ ሰባት ከፍ አሉ። ዘንድሮ ደግሞ እንዳያችሁት በዐሥር የተለያዩ ዘርፎች የሽልማት ዕውቅና ተሰጥቷል። የዘንድሮው ሽልማት ከጥቆማው ጀምሮ ረጅም ጊዜ፤ ዐሥራ አንድ ወራት ያክል ጊዜ ወስዷል። ሥራው ብቻ ሳይሆን በአገሪቱ የነበሩ የተለያዩ ክስተቶች (ለምሳሌ ምርጫና ሊቢያ ላይ በወገኖቻችን ላይ የደረሰው አሰቃቂ ሁኔታ) ጊዜ ወስደውብናል። ዘንድሮ የተጠቆሙት እጩዎች ብዛት ወደ 220 ሲሆን ይህም ካለፉት ጊዜያት አንጻር ስናየው የተሻለ ተደራሽ ነበር ማለት ይቻላል። ከሽልማት ሥነ ሥርዓቱ በኋላ የኮሚቴው አባላት ብርቱና ደካማ ጎኖችን ተገናኝተን ገምግመናል። የሥራውን ጥራት ለመጠበቅ የተደረገው ጥረት፣ የሽልማት ዘርፎቹ ወደ ዐሥር ከፍ ማለታቸው፣ የዳኞቹ ጥንካሬ፣ በተለያዩ አካባቢዎችን ለማካተት የተደረገው ሙከራ፣ በመጨረሻም የሽልማት ሥነ ሥርዓቱን ለማሳመር የተሠራው ሥራ በጠንካራ ጎንነት ታይቷል።

> “ግብጽ ውስጥ አንድም መነኩሴ ከተማ ውስጥ አይታይም፤ ከልክል ነው። እኛ ጋ ግን መርካቶ የምታየው መነኩሴ ብዙ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በቂ የሆነ ዕጩ አግኝተናል ብለን አሁንም አናምንም። ይህ ችግር በተወሰነ መልኩ እስከተወሰኑ ዓመታትም ላይፈታ ይችላል። እንዳልኩት በአገሪቱ የነበሩ የተለያዩ ክስተቶች በያዝነዉ ጊዜ ሥራችንን እንዳናከናውን አድርገውናል። ሌላው በእኛ አገር አንዳንድ መረጃዎችን ለማገኘት ከእኛ አቅም በላይ የሆኑም ነበሩ። በሽልማት ሥነ ሥርዓቱ ላይ መከናወን የነበረባቸው ግን በምንፈልገው መጠን ያላደረግናቸው ነገሮች አሉ። ነጋሪት ለማገኘት አስቸጋሪ ሆኖብን ነበር። ከሂደቱ የተማርነው መርሐ ግብሩ ከመድረሱ በፊት አስቀድመን ማስተካከል እንዳለብን ነው።

በዚህ ዓመት ዋነኛ ሥራችን ሽልማቱን ተቋማዊ የማድረግ ሥራ ነው። ቢቻል በመንግሥት በጎ አድራጎት ማኅበራት ኤጀንሲ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሆኖ እንዲመዘገብ ካልተቻለ ደግሞ ሌሎች ሕጉ የሚፈቅዳቸው አሠራሮችን ተከትሎ ተቋማዊ ማድረግ ያስፈልጋል ብለን እየተንቀሳቀስን ነው። ሌላው ጥናት ካጠናን በኋላ ‹‹ባሉት ዘርፎች እንቀጥል ወይስ ተጨማሪ ዘርፎች ያስፈልጋሉ?›› የሚሉ ነገሮችን እንወስናለን። በተቻለ መጠን የክልል ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎችን በመጠቀም የክልል ተደራሽነትን ለመጨመር ዕቅድ ይዘናል።

**<<በሰላም ዘርፍ ለመሸለም ዕቅድ ብንይዝም የተጠቆመ እጩ ባለማግኘታችን መሸለም አልቻልንም>> የሚል ነገር ቀርቦ ነበር። በእርስዎ ግምገማ ዕጩ ያልተገኘው ለምን ይመስልዎታል? ዕጩ አለመገኘቱስ የሚያመለክተው ነገር ይኖር ይሆን?**

በሰላም ዘርፍ የተጠቆሙ ዕጩዎች ነበሩ። ነገር ግን በቁጥር ደረጃ በቂ አልነበሩም። አንድ ወይም ሁለት ሰው ብቻ ይዞ ወደ ውድድር መግባት አስቸጋሪ ነበር። አንዳንዶቹ የተጠቆሙት ዕጩዎችም በጭራሽ ከሰላም ጋር የሚገናኙ አልነበሩም። ስለዚህ እኛ ያየነው በዚህ ዓመት የሰላም ሽልማቱን ትተን በዚህ ጉዳይ በደንብ ሠርቶ ቀጣይ የሽልማት ዘመን ላይ ማወዳደር እንደሚሻል ነው። በኔ ግምት በቂ ዕጩ አለመቅረቡ ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ያሳየናል። አንደኛው ‹‹ሰላም ምንድነው?›› በሚለው ትርጉም ላይ በእኛና በዕጩ ጠቋሚዎች መካከል መግባባት አልነበረም ማለት ነው። ሁለተኛው ሰላም በተለይም ግጭቶችን በመፍታት ሂደት ለአገራቸው ሰላም የሚጥሩ ግለሰቦችን የሰጠናቸው ዋጋ አነስተኛ እንደሆነ እንረዳለን። ለሰላም የሠሩ ሰዎች በአገራችን አሉ። ግን ብዙዎቻችን እንደሌሎች ታዋቂ ግለሰቦች የሚገባቸውን ክብር አልሰጠናቸውም።

**እስኪ ደግሞ እንደቤተ ክርስቲያን ተመራማሪና እንደ አገልጋይ ይመለከተወታል ብለን ስለምናስበው ርእሰ-ጉዳይ አንዳንድ ነጥቦችን እናንሳ፤ እንደሚያውቁት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያለው ሙስና በብዙ መገናኛ ብዙኃን ሲዘገብ ቆይቷል። ጉዳዩ ካመት ዓመት ከመሻሻል ይልቅ ተባብሶ እንደቀጠለ ነው። ለመሆኑ ምዕመናንን ያስተምራሉ፣ ምሳሌ ይሆናሉ የሚባሉት አባቶች ራሳቸው በዚህ አሳፋሪ ተግባር ላይ መዘፈቃቸው እንዴት ይታያል? በዚህ ይዞታው የሚያስተምሩት ሕዝብስ እንዴት ሊሰማቸውና ሊቀበላቸው ይችላል? ለቤተ ክርስቲያኒቱስ አደጋ አይደለምን?**

እንደኔ መረዳትና ጥናት ቤተ ክርስቲያን አሁን የተጋረጠባት አደጋ ከሁለት ነገሮች የመጣ ነው። አንደኛው ቤተ ክርስቲያኒቱ ዘመናዊውን ዓለም

# እንግዳ

የተቀላቀለችበት መንገድ የፈጠረው ችግር ነው። የጥንቷ ቤተ ክህነት በተለይም ከ1950ዎቹ በፊት የነበረችው ቤተ ክህነት ከቤተ መንግሥቱ ጥግ ነበረች። አብዛኛው ሥራዋ መሬት ተኮር ነበር፤ ወደ ዘመናዊው የንግድ ዓለም አልገባችም ነበር። ለምታስተዳድረው መሬትም ከገበሬው የወጡት ቀሳውስት በቂ ነበሩ። እንዴት መሬት ማስተዳደር እንዳለባቸው በደንብ ያውቁ ነበር። በተጨማሪም በወቅቱ ለነበሩት ሥራዎች የሚበቃ የሰው ኃይልም ነበራት። ዘመናዊ ቤተ ክህነት ሲቋቋም ግን ለዘመናዊ ሥራ የሚሆን የሰው ኃይል አላደራጀችም። ለምሳሌ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ አያያዝ (Church Accounting) ትምህርት በየትኛው የቤተ ክርስቲያን ተቋም አይሰጥም። ዘመናዊ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ትምህርት ቤተ ክርስቲያኒቱ አትሰጥም። የቀድሞው ፍትሐ ነገሥት ቢኖርም በቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ ሕግን የሚመለከት ትምህርት አሁን አይሰጥም። የንግድ ተቋማቷን ያለምንም ሙያ ነው የምታስተዳድረው። ስለዚህ ‹‹ለምን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር ተፈጠረ?›› ብለን ስንነጋገር ችግሩ ያለው ከዚሁ ውስጥ ነው። ድጓው ውስጥ፣ ቅኔው ውስጥ፣ ቅዳሴው ውስጥ፣ ማህሌቱ ውስጥ፣ ሰዓታቱ ውስጥ ምንም ችግር የለም። ለዚህ የሚሆን በቂ የሰው ኃይልና በቂ ልምድ አላት። ዘመናዊ ተቋም የሚያስፈልጋት ዘመኑ ላመጣቸው አዳዲስ ዕውቀቶች ነው። ያልተማሩ ወይም ለነዚህ ዘመናዊ አሠራሮች ሙያ የሌላው ሰዎች ሲሰማሩ ክፍተት ተፈጠረ። በቢሊዮን የሚቆጠር የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብት የሚመሩ ሰዎችን ብትመለከት ለቦታው የሚመጥን ዕውቀት የላቸውም። ድጓ፣ ቅኔ፣ አቋቋም ወዘተ. ተምረህ ቢሊዮን ገንዘብ ልታንቀሳቅስ አትችልም። የሙያ ክፍተት ይፈጥራል።

ሁለተኛው ችግር ደግሞ የቤተ ክርስቲያኒቱ የፖሊሲ ችግር ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ ‹‹ምን ተግባር ላይ ነው የምሰማራው? ምን ላይ ነው የማልሰማራው? የትኛውን ነው የምሠራው? የትኛውን ነው የማልሠራው? የትኛው ይገባኛል? የትኛው አይገባኝም?›› የሚል ፖሊሲ ማውጣት አልቻለችም። ለምሳሌ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ከምናያቸው የንግድ ተቋማት ውስጥ አብዛኞቹ ሱቆች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ‹‹በእንዲህ ዓይነት ንግድ ውስጥ መግባት አለባት? የለባትም?›› ያከራክራል፤ ፖሊሲ የላትም። ብዙ ትምህርት ቤቶች ከፍታለች፤ የትምህርት ፖሊሲ ግን የላትም። የጤና ተቋማት ከፍታለች፤ የጤና ፖሊሲ ግን የላትም። ሌሎችንም ተቋማት ከፍታለች፤ ነገር ግን ምንም ፖሊሲ የላትም። የቀድሞ ትምህርት ቤቷችን የምታስተዳድርበት እኮ ያልተጻፈም ቢሆን የተለመደ አሠራር አላት። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያኒቱ አሁን የምትወቀስበት እነዚህን ዘመኑ አምጥቶ የጨመረባትን ነገሮች በአግባቡ ማስተናገድ ባለመቻሏ ነው እንጂ ነባርና ልምድ ያካበተችባቸወን ዘርፎች በሚገባ ነው የምትከውናቸው። ይህ ምን አስከተለ? በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የሚንጠላጠሉ ሰዎችን ፈጠረ።

**አሁን ያለው ችግር ግን የዕውቀት ችግር ብቻ ነው ማለት ይቻላል?**

የዕውቀት ችግር ብቻ አይደለም። ወደዚህ ቦታ የምታሰማራቸዉን ሰዎች መርጠህ አዘጋጅተህ የማሰማራት ችግር አለ። ይህ ተቋማዊ ችግር ነው፤ የቤተ ክህነት ተቋማዊ ኪሳራ ነው። ዛሬ አንድ መርጌታ ልቅጠር ብትል ችግር የለም። አንድ አገልጋይ ካህን ለመቅጠር ብትል በቂ የሰው ኃይል አለ። ነገር ግን በሥነ ምግባሩ የተመሰገነ፣ በቂ ዕውቀት ያለው እያልክ በመስፈርት የቤተ ክርስቲኒቱን ሀብት የሚያስተዳድር ሰው ለመቅጠር ችግር ነው። አይገኝም። አንድ ሰው ቅኔ ማህሌት ቁሞ ቢያበላሸዉ በሁሉም አቅጣጫ ‹‹እንደሱ አይደለም!›› የሚለው ሰው ብዙ ነው። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያኒቱ ዘመናዊ አስተዳደር ሲበላሽ ‹‹እንደሱ አይደለም፤ አይሆንም!›› የሚል ሰው ጠፍቷል። ለዚህ የሚሆን በቂ ዕውቀትና በቂ ሥርዓት አልተዘረጋም። ያለ ፋይናንስ ፖሊሲ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚያስተዳድር ተቋም ከቤተ ክህነት ውጭ የለም። አሁንም እኮ እንደ ድሮው ሞዴል 16፣ ሞዴል 30 እየተባለ ነው የሚሠራው። በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኮምፒዩተር ዘመን የዚህ ዓይነት አሠራር እንዴት ያስኬዳል? ሥርዓቱ በራሱ ለቁጥጥር ሳይሆን ለመብላት የተመቸ ነው። እንዲበላ ተብሎ የተዘጋጀ አሠራር እኮ ሆኖ አይደለም። ግን ይህ በዘመኑ ዘመናዊ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ዘመኑ ተሻሽሏታል። ምንም ያህል ጥሩ ሰው ብትሆን በዚህ መዋቅር ውስጥ ከሠራህ ሥርዓቱ በራሱ ያበላሽሃል።

> ቤተክርስቲያን አስተማሪ ናት፤ መካሪ ናት፤ ለሕዝብ ደህንነት የቆመች ናትና የመጀመሪያ ሥራዋ አብያተ ክርስቲያናትን ማስፋፋት ነው። ቀጥሎ ትምህርት ቤቶችን መሥራት፣ የአረጋውያንን መጦሪያ መሥራት፣ የድሆችን መመገቢያ መሥራትና ሌሎችንም ማከናወን ነው የነበረባት። ‹‹እነዚህን ነገሮች ለመሥራት ገንዘብ ያስፈልገኛል›› ካለች ቀጥሎ የሚመጡ ነገሮች ናቸው ››

መንግሥት የግዥ ሥርዓቱን በብር መጠን በቀጥታና በጨረታ ማስታወቂያ የሚፈጽምበት መመሪያ አለው። ይህም ሆኖ ስላልተቻለ እንደገና ማዕከላዊ የግዥ አሠራር አምጥቷል። ቤተ ክህነት ውስጥ ግን ዝርዝር የጨረታ አሠራር፣ ዝርዝር የግዥ ሂደት አሠራር አታገኝም። ይህ ሁሉ ግንባታ እየተከናወነ ግንባታ የሚመራ መምሪያ እንኳ የላትም። የግንባታውን ጥራት የሚቆጣጠር፣ ግንባታው የሚሠራው በትክክለኛ ጨረታ ነው ወይ? የሚሠሩ ሥራዎች ከቤተ ክርስቲያኒቱ ፖሊሲዎች ጋር አብረው የሚሄዱ ናቸው ወይ? ወዘተ. ብሎ የሚያይ አካል እኮ የለም። ያም ተነስቶ ‹‹ሱቅ እከፍታለሁ›› ቢል ከልካይ የለውም፤ ‹‹ሱቅ ሳይሆን ጉልት ገበያ›› እከፍታለሁ የሚለውም ከልካይ የለውም።

**ቤተ ክርስቲያኒቱ በአንዳንድ ዘርፎች ለምሳሌ በሕንጻ ግንባታ፣ በቤተሰብ ጉዳይ ወዘተ. የበርካታ ዓመታት ልምድ ባለቤት ናት። ነገር ግን ያሳየችዉ ለውጥ የለም። እነዚህ ችግሮች ሲከሰቱ የሚመለከት ሰው እንዴት ጠፋ?**

በነገራችን ላይ በ1950ቹ አቡነ ቴዎፍሎስ ጀምረውት ነበር። ግን ሕንጻዎቹ ተሠርተው አልቀው ገና ቤተ ክርስቲያኒቱ ማስተዳደር ሳትጀምር ደርግ ወረሳቸው። በዚህ ምክንያት ልምዱ ሊካብት አልቻለም። አብዛኛዎቹ ሕንጻዎች ደግሞ በበጎ አድራጎት ተሠርተው የተበረከቱ ነበሩ። የተወረሱት ሕንጻዎች ሲመለሱ እነርሱን የሚያስተዳድር መምሪያ ብትከፍትም በየአጥቢያው ያሉ ሕንጻዎችን የሚያስተዳድር አካል ግን አልመደበችም። ዘመናዊውን ቤተ ክህነት ስታቋቁም የዕውቀትና የልድም ክፍተት ነበረባት። እስከአሁን ድረስ ያልተሞላው ችግር እርሱ ነዉ። ለምሳሌ አንድ በሠራተኛ አስተዳደር በቤተ ክህነት የተመደበና አንድ ደግሞ በመንግሥት በሠራተኛ አስተዳደር የተመደበ ሰው እኩል ዕውቀት የላቸውም። በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሙያው ልምድና ችሎታ ያለው ሰው ይቀጠራል። ቤተ ክህነት ግን እንደዚህ ያለ አሠራር የለም።

**ግን እኮ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤቶች መምህራን ለመቅጠር በመስፈርት ማስታወቂያ ሲያወጡ እናያለን!**

ዕውቅና ለመስጠት ትምህርት ሚኒስቴር ስለሚያስገድዳቸው ነዋ። ግን ‹‹አንድ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤት ምን መምሰል አለበት?›› ያልን እንደሆነ ‹‹ይህን የሚመልስ›› ብሎ የሚያስቀምጥ ፖሊሲ የለም። አሜሪካ ብትሄድ የካቶሊክ ትምህርት ቤቶች በደንብ ይታወቃሉ። ግልጽ የሆነ መመሪያና ፖሊሲ አላቸው። የእኛ ግን ምንም የለም። ምኑ ነው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤት ያስመሰለው? ምንም የለም። ትምህርት ሚንስቴር ይቆጣጠራቸዋል እንጅ እኮ የቤተ ክህነት ትምህርት ዘርፍ የሚባል ተቆጣጣሪ ድርጅት የላትም።

**በቤተክርስቲያን ውስጥ የሙስና ጉዳይ ትልቅ መነጋገሪያ እየሆነ መጥቷል። መንፈሳዊ መሪዎችና አባቶች በዚህ ዓይነት ምግባር ተዘፍቀዉ እንዴት ነው ምዕመኑን መምራት የሚችሉት? በዚህ ይዞታቸዉ የሚያስተምሩት ሕዝብስ እንዴት ሊሰማቸዉና ሊቀበላቸዉ ይችላል?**

እሱ ከባድ ነው። ምዕመኑን ከቤተ ክርስቲያኒቱ የመነጠል አደጋም አለው። ምዕመኑ አባቶቹን ማመን ያቅተዋል። ነገ አሥራት በኩራቱን ለመክፈል፣ ኑዛዜውን ለንስሀ አባቱ ለመናገር ወዘተ. ይቸግረዋል። ለዚህ ነው ቤተክርስቲያኒቱ መንቃት ያለባት። አጠቃላይ ተቋማዊ ለውጥ ያስፈልጋታል። ቤተ ክህነታዊ ለውጥ ያስፈልጋታል። መምሪያዎቿን እንደገና የማየት፣ ፖሊሲ ማርቀቅ ያስፈልጋታል። መዋቅራዊ አሠራሩ በደንብ እንደገና መፈተሽ አለበት። ጥብቅ፣ ግልጽና አሳታፊ የሆነ አሠራር መዘርጋት አለበት። ለምሳሌ አጥቢያዎች ኦዲት መደረግን መልመድ አለባቸው። በውጭ ኦዲተር ኦዲት ተደርገው መቅረብ አለባቸው። ሕዝቡ ለሰጠው ገንዘብ ጠያቂ ስለሚሆን ለሕዝቡ በግልጽ መቅረብ አለበት። ይህ አለመሆኑ ደካማ አሠራርን ተጠቅመው መቦጥቦጥ የሚፈልጉ ሰዎችን ይስባቸዋል። ጠንካራ ሥርዓት ሲኖር በዚህ መጠቀም የሚፈልጉ ሰዎች አይቀርቡም፤ ይፈሩታል።

**አሁን ባለው ሁኔታ ለውጥ የሚመጣ ይመስልዎታል?**

እኔ በሂደት ለውጡ በሁለት መንገድ ይመጣል ባይ ነኝ። ወይ ውስጥ ያሉት አባቶች ችግሩን በደንብ ተረድተውት ዘላቂ መፍትሔ ለመፈለግ ይነሳሉ። ካልሆነ ደግሞ ወቅቱ ያስገድዳል። እንዲህ ሆኖ መቀጠል አይቻልም። የሆነ ጊዜና ቦታ ላይ ግጭት ይፈጠራል። ግጭቱን ቀድመህ ከደረስክበትና ከፈታኸው ጥሩ ነው። ካልሆነ ግን ለውጡም ግጭቱም ይመጣል። ግን ኪሳራ ያስከትላል። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ትውልዱም መሸከም የማይችልበት ደረጃ ላይ ይደርሳል። ግን የዚህ ዓይነቱ ለውጥ አስጊ ነው፤ ጥሩ ለውጥ አይደለም። ለውጡ ከተቋሙ ከራሱ ቢመጣ ነው ጥሩ የሚሆነው።

ቤተ ክርስቲያኒቱ በገንዘብ እጅግ ሀብታም እንደሆነች ይታወቃል። ነገር ግን ‹‹ይህን ያህል ሀብት አላት›› ተብሎ ሪፖርት አይቀርብም። የግልጽነት አለመኖሩ ደግሞ ነገሮችን ይበልጥ እያወሳሰባቸው ነው። በእርስዎ አስተያየት ሪፖርት የማይቀርብበት ምክንያት ምንድን ነው?

እውነት ነው፤ አጠቃላይ ሀብቷን የሚመለከት ሪፖርት ቀርቦ አያውቅም። አጠቃላይ ሀብቷን ሪፖርት ለማቅረብ የሚያስችል ሥርዓትም የላትም። ይህን የሚመራ ትልቅ የፋይናንስ ተቋም ያስፈልጋል። መንግሥት እኮ ይህን ያክል ገንዘብ የሚያስተዳድረው ገንዘብ ሚንስቴር የሚባል ተቋም ይዞ ነው። ቤተ ክህነት እኮ ገንዘብ ሚኒስቴርን የሚስተካከል ትልቅ የፋይናንስ ተቋም ያስፈልጋታል። ከ35,000 በላይ አብያተ ክርስቲያናት ያሏት፣ ከ40,000 በላይ ካህናት ያሏት፣ ከ1,100 በላይ ገዳማት ያሏት ቤተ ክርስቲያን ሀብት የሚያስተዳድር የገንዘብ ተቋም ያስፈልጋታል።

**ጎሰኝነቱም ሌላው የቤተ ክርስቲያን ፈተና ነው ይባላል። ይህስ እንዴት ይታያል?**

እኔ ‹‹ጎሰኝነቱን የበለጠ እንዲያብብ ያደረገው የተንሰራፋው ሙስና ነው›› ነው የምለው። አካባቢያዊነት በአገራችን የኖረ ነው። ሆኖም ሙስናው ላይ ስትቆም አካባቢያዊነት ወደ ጎሳኝነትና ጠባብነት ያድጋል። ሙስና ላይ ስትቆም የምታምናቸው ሰዎችን ትፈልጋለህ። ስለዚህ ጎሰኝነቱ የቆመው ሙስናው ላይ ባይ ነኝ።

**በመርህ ደረጃ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ገንብታ የንግድ ተቋማትን ከማስፋፋትና ትምህርት ቤት ከማቋቋም የትኛውን ብትሠራ ተመራጭ ይሆናል?**

መሆንማ የነበረበት ቤተክርስቲያን አስተማሪ ናት፤ መካሪ ናት፤ ለሕዝብ ደህንነት የቆመች ናትና የመጀመሪያ ሥራዋ አብያተ ክርስቲያናትን ማስፋፋት ነው። ቀጥሎ ትምህርት ቤቶችን መሥራት፣ የአረጋውያንን መጦሪያ መሥራት፣ የድሆችን መመገቢያ መሥራትና ሌሎችንም ማከናወን ነው የነበረባት። ‹‹እነዚህን ነገሮች ለመሥራት ገንዘብ ያስፈልገኛል›› ካለች ቀጥሎ የሚመጡ ነገሮች ናቸው። እንደምታዩት በአገራችን አብያተ ክርስቲያናቱን የንግድ ድርጅቶች ውጠዋቸዋል። ስለዚህ ድሮ ከሩቅ የምትሳለመውን አሁን ከሩቅ መሳለም አትችልም። የትኛው ነው የገዘፈ? ግዝፈት ትኩረትን ያሳያል። ቤተክርስቲያኒቱ ትንሽ ሆና የንግድ ሕንጻው ግን ግዙፍ ሆኖ ትኩረታችን የትኛው ላይ ነው? ይህ ሁሉ ቀጣዩ ትውልድ ለሚጠይቀው ጥያቄ ከባድ መልስ ነው።


**የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ፖፕ ወደኢትዮጵያ ለይፋ ጉብኝት እንደሚመጡ ታውቋል። ሁለቱ ቤተክርስቲያናትና አገሮች በብዙ መልኩ የተሳሰሩ ቢሆንም የሚገባውን ያህል ሲደጋገፉ፣ አንዱ ከአንዱ ሲማርና ተመክሮ ሲቀስም አይስተዋልም። በዚህ ላይ ምን አስተያየት አለዎት?**


ኢትዮጵያና ግብጽ በተፈጥሮ፣ በባህልና በእምነት የማይነጣጠሉ አገሮች ናቸው። በተፈጥሮ አባይ የሚባል ቆርጠን የማንጥለው ሁለቱንም አገሮች የሚያጠጣ ወንዝ አለን። በባህል የግብጽ ባህል በእኛ ውስጥ አለ፤ የእኛም ባህል በግብጽ ውስጥ ተጽዕኖ ፈጥሯል። ‹‹Egypt the Doughter of Ethiopia›› የሚለውን መጽሐፍ ብታነቡ የእኛ ባህል በግብጽ ሥልጣኔ ውስጥ ምን ያክል ዋጋ እንደነበረው ትገነዘባላችሁ። በእምነት ደረጃ ያየነው እንደሆነ ክርስትናም እስልምናም በሁለቱ አገሮች አሉ። የግብጽ ቤተክርስቲያን ደግሞ 111 ጳጳሳትን ወደ ኢትዮጵያ ልካለች። ብዙ ቅዱሳን ከኢትዮጵያ ወደ ግብጽ ሂደዋል፤ ከግብጽም ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል። ብዙ መጻሕፍት ከእኛም ወደነሱ ሄደዋል፤ ከነሱም ወደኛ መጥተዋል። ስለዚህ አንድነቱ እጅግ ከፍተኛ ነው። ግን በሚገባ አልተጠቀምንበትም። እንዲያውም ሽኩቻው ነው የሚበልጠው። ግብጾችም ከእኛ እኛም ከግብጾች የምንማረው ብዙ ነገር አለ። ዘመናዊውን ነገር የግብጽ ቤተክርስቲያን እንዴት ነው እያስተዳደረችው ያለው? ቅድም ያነሳናቸውን ጉድለቶች ግብጾች እንዴት ነው የሚያስተናግዷቸው? ከእነርሱ የምንማራቸው ነገሮች ናቸው። ጥንታዊውን እምነት እንዴት ነው መያዝ የሚቻለው? ግብጾች ከእኛ የሚማሩት ነዉ። ስለዚህ ጥንቱን ከእኛ ዘመኑን ከእነርሱ ልምድ መያዝ ያስፈልጋል። ሲኖዶሳችን ከሲኖዶሳቸው ልምድ መውሰድ ይኖርበታል። ለምሳሌ የምርጫ ሂደታቸውን በሚመለከት ልምድ መውሰድ ያስፈልጋል። መነኮሳቱን የሚይዙበትን መንገድ ልምድ መውሰድ ያስፈልጋል። ግብጽ ውስጥ አንድም መነኩሴ ከተማ ውስጥ አይታይም፤ ክልክል ነው። እኛ ጋ ግን መርካቶ የምታየው መነኩሴ ብዙ ነው። ስለዚህ ግንኙነቱን ከፕሮፖጋንዳ የዘለለ ብናደርገው እንጠቀማለን። አሁን የምናየው ግን ብዙ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ይመስላል። ከዕለታት አንድ ቀን እንሄዳለን፤ ከዕለታት አንድ ቀን ይመጣሉ። እሱ አይደለም የሚጠቅመን። ከዚያ ያለፈ ልምድ የምንለዋወጥበት መሆን አለበት። የእነርሱ ገዳማውያን ከእኛ ገዳማውያን ጋር የሚኖሩበት የእኛ ገዳማውያን ከእነርሱ ገዳማውያን ጋር የሚኖሩበት፣ ተማሪዎቻችን ከተማሪዎቻቸው ልምድ መለዋወጥ የሚችሉበትን መንገድ መቀየስ ያስፈልጋል፤ ይቻላልም።

# የዜጎች ድምጽ

(በዚህ ዐምድ ኢትዮጵያውያን የማኅበራዊ ድረ ገጽ ተጠቃሚዎችን የሚያወያዩና የሚያከራክሩ አንኳር ጉዳዮች ተመርጠው ይቀርባሉ)

## መብራቱ በላቸው







ባሳለፍነው ዓመት መጨረሻ ቀናት ከተከናወኑና ትኩረት ከሳቡ ዐቢይ ጉዳዩች ውስጥ የዞን 9 ጦማሪያን ለ37ተኛ ጊዜ የመቀጠራቸው ዜና ተጠቃሽ ነው:: ዜናውን ተከትሎ ብዙ ወዳጆቻቸው፤ ጓደኞቻቸውና አድናቂዎቻቸው በተለያዩ ማኅበራዊ ድረ ገጾች ቁጭታቸውን፣ ትችታቸውንና ትዝብታቸውን ገልጸዋል:: ከነዚህ ውስጥ ‹‹Zone9›› በሚል የፌስቡክ ግጽ ላይ እንዲህ የሚል ድምጽ ተስተጋብቷል ‹‹በአጠቃላይ ለ36ተኛ ጊዜና ለብይን ለ4ተኛ ጊዜ ተቀጥሮ የነበረው የዞን 9 ጦማርያን ጉዳይ በድጋሚ ለመስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም. ተቀጠረ:: በነሶልያና ሽመልስ የክስ መዝገብ እስከዚህ ጊዜ ድረስ በተደጋጋሚ የተላለፈው የብይን ጥበቃ በድጋሚ ‹‹ዳኞች አልተሟሉም›› በሚል ሰበብ ለ37ተኛ ጊዜ ተቀጥሯል:: ‹‹በዳኞች አለመሟላት የተነሳ ችሎቱን ማስቻል አልችልም›› ብለው በቢሮ ተከሳሾችንና ጠበቆችን የጠሩት ዳኛ ዘሪሁን ‹‹ብይኑ ቢሠራም ለማሳወቅ ሁሉም ዳኞች መገኘት ስላለባቸው ለመስከረም 27 ቀን ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥተናል›› ብለዋል:: ውሳኔው ተከሳሾችን፣ ቤተሰቦቻቸውንና ውሳኔውን ሲጠብቁ የነበሩ ብዙ ወዳጆቻቸውን በከፍተኛ ደረጃ ያስከፋ ነበር:: ከአንድ ወር በኂላ በመደበኛው የፍርድ ቤት መከፈቻ ጊዜ የተቀጠረው ችሎት ተከሳሾች መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ ይሰናበቱ ወይስ ይከላከሉ የሚለውን ውሳኔ ያነባል ተብሎ ይጠበቃል::

### የዞን 9 ጦማር

‹‹በአሳፋሪው የፍትሕ ሥርዓትና በሥራ አስፈጻሚው በሚዘወሩት ዳኞች እንደ ተከሳሽም ሆነ እንደ አገር ማፈራችንን እያሳወቅን ይህ በውጤታማ እና ሰላማዊ ወጣቶች ሕይወት ላይ መቀለድ፣ በታሪክም ሆነ በወደፊትዋ ፍትሓዊ ኢትዮጵያ ፊት የዳኞችን አንገት የሚያስደፋ ተከሳሾችን ደግሞ የሚያኮራ ተግባር ሆኖ እንደሚታወስ በእርግጠኝነት እንናገራለን:: የዞን 9 ጦማርያን በአምባገነን አገዛዝ የሚዘወሩ የጭቆና እጆች የማያንበረክኳቸው ኩሩና ነጻ ወጣቶች ናቸው::›› በማለት በአጠቃላይ የነበረውን ሂደትና ሂደቱ ያስከተለውን የቁጭት ስሜት ያስነበበው ‹‹Zone9›› የፌስቡክ ገጽ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ተከትሎ ‹‹የዞን 9 የ2007 ዓ.ም. የእስር መስመር›› በሚል ርእስ ‹‹ሁለተኛ እንቁጣጣሻቸውን በቅሊንጦ እስር ቤት ያከብራሉ›› ሲል የሚከተለውን ሰፋ ያለ ሐተታ አቅርቧል::

የዞን 9 ጦማርያን ከታሰሩ አንድ ዓመት ከአምስት ወራት የተቆጠረ ሲሆን ወዳጅ ጋዜጠኞችን ጨምሮ ከጠቅላላው ዘጠኝ እስረኞች መካከል አራት ጦማርያን አሁንም በእስር ላይ በመሆናቸው ሁለተኛ እንቁጣጣሻቸውን በቅሊንጦ እስር ቤት ያከብራሉ:: ባለፉት አንድ ዓመት ከአምስት ወራት 36 ጊዜ ፍርድ ቤት የተመላለሱ ሲሆን እስራቸው እና የፍርድ ሂደቱ በ2007 ዓመተ ምህረት ምን ይመስል እንደነበረ በመጠኑ እናያለን::

> በዓመቱ የመጨረሻ ሳምንት የመጨረሻ የእስር ሳምንታቸው ይሆናል ተብሎ ተስፋ ቢደረግም ፍርድ ቤቱ ዳኞች አልተሟሉም በሚል ሌላ ሰበብ ሁለተኛውን እንቁጣጣሻቸውን በእስር እንደሚያሳልፉ ያረጋገጠውን የ31 ቀን እንዲቀርቡ በማዘዝ ለመስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም 37ኛውን ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል

### የዞን 9 የእስር መስመር

የዓመቱ መጀመሪያ ጦማሪ በፍቃዱ ኃይሉ በጻፈው ‹‹የቀድሞው አብዮተኛ ኑዛዜ›› ተጀመረ:: ጽሑፉ በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች በዞን 9 ጦማር ላይ ታትሟል:: በጥቅምት ወር 2007 ዓ.ም. የሕግ የበላይነትና ጸረ ሽብር ሕጉ ሲገመገም የሚለው የጸረ ሽብር ሕጉና የአሁኗ ኢትዮጵያ ያላቸውን ግንኙነት እንዲሁም ሕጉ ምን ተጽዕኖ እንዳለው የሚያሳየው ልዩ ሪፓርታዥ

ተዘጋጀ:: ጥቅምት 11 ቀን 2007 ዓ.ም. በእስር ላይ ይገኙ የነበሩትን ጦማሪት ማህሌት ፋንታሁንና ጋዜጠኛ ኤዶም ካሳዬን የእስር ቤት አያያዝ አስመልክቶ የቀረበውን አቤቱታ ለማየት ችሎቱ ተሰየመ:: በዕለቱ እስር ቤቱ የተለየ አያያዝ መኖሩን ክዶ የተከራከረ ሲሆን ፍርድ ቤቱም እንደተለመደው ‹‹እንዳይደገም›› በሚል የማረሚያ ቃል የዕለቱን ሂደት አጠናቀቀ:: ከጥቅምት 12 ቀን ጀምሮ ለአንድ ሳምንት የሚቆይ የዞን 9 ጦማርያን 6 ወር የእስር ቆይታን አስመልክቶ የቤተሰቦቻቸውን ድካም የማገዝ የገንዘብ ማሰባሰብ ሥራ በዞን 9 ጦማርያን ወዳጆች አማካኝነት በተሳካ ሁኔታ ተከናወነ:: ጥቅምት 25 ቀን ጦማርያኑ ለዐሥረኛ ፍርድ ቤት ቀረቡ::

ሕዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም. የዞን 9 ጦማርያንና ጋዜጠኞች ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ በተለያዩ ሚዲያዎች ላይ ሲቀርቡ የሚሰጡት አስተያየት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን የጣሰ መሆኑን አስመልክተው ደብዳቤ ጻፉ:: ደብዳቤው የተከሳሾችን በሕግ ፊት ንጹህ ሆኖ የመቆጠር መብት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እየጣሱ እንደሆነና ከዚህ ድርጊታቸው እንዲታረሙ የሚጠይቅ ነበር:: ሕዳር 3 ቀን ጦማርያኑና ጋዜጠኞቹ ለ11ኛ ጊዜ ፍርድ ቤት የቀረቡ ሲሆን በዚህ የፍርድ ቤት ውሎ አቃቤ ሕግ በአምስት ጉዳዮች ላይ ክሱን እንዲያሻሽል ትእዛዝ ተሰጥቶታል:: (‹‹ሊፈጽሙ ነው›› የተባለውን የሽብር ወንጀል በግልጽ ማስቀመጥ፣ ‹‹ቡድኑ›› እየተባለ የተቀመጠው ቡድን ማን እንደሆነ በግልጽ ማስቀመጥ፣ የሥራ ክፍፍልን አስመልክቶ የተጠቀሰውን በግልጽ መስቀመጥ፣ ‹‹ተላከ›› የተባለውን አርባ ስምንት ሺህ ብር አስልክቶ በግልጽ ከማን እንደ ተላከ ማስቀመጥ፣ ‹‹ሥልጠና›› የተባሉት ምን እንደሆኑ በግልጽ ማስቀመጥ እና የሽብር ሥልጠና ሰጪ ድርጅቱን በግልጽ ማስቀመጥ ይገኙበታል) ሕዳር 17 ቀን የዋስትና መብትን አስመልክቶ በጦማርያኑ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረበው ይግባኝ ውድቅ ተደርጎ በእስር መቆየታቸው እርግጥ ሆነ:: ሕዳር 24 ቀን ተሻሻለ የተባለው ክስ በድጋሚ ለፍርድ ቤት ቀረበ:: ጠበቆች ተሻሻለ በተባለው ክስ ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ተነገራቸው:: ተሻሻለ የተባለው ክስ ‹‹ቡድኑ ግንቦት 7 ነው›› ከሚለው ውጪ ምንም ዓይነት መሻሻል ሳይደረግበት ነበር ለፍርድ ቤት የቀረበው::

ታህሳስ 7 2007 ዓ.ም. ጦማሪ ዘላለም ክብረት በእንግሊዘኛ የጻፈው የናፍቆት ደብዳቤ ታተመ:: ታህሳስ 9 ቀን የጦማሪ አቤል ዋበላ ‹‹ሕልም እንደሆነ አይታሰርም›› የሚለው ተወዳጅ ጽሑፍ በዞን 9 ጦማር ላይ ታተመ:: ታህሳስ 27 ቀን ጦማርያኑና ጋዜጠኞች በድጋሚ ፍርድ ቤት ቀረቡ:: ፍርድ ቤቱ ክሱ እንዲሻሻል ታዞ ነገር ግን በተለያዩ አራት ጉዳዮች ላይ አሁንም ባለመሻሻሉ በድጋሚ እንዲሻሻል ሁለተኛ ትእዛዛ ሰጠ::

ጥር 6 የዞን 9 ጦማርያንና ጋዜጠኞች በድጋሚ ፍርድ ቤት ቀረቡ:: በዕለቱ አቃቤ ሕግ በድጋሚ አሻሻልኩት ያለውን ክስ ይዞ ቀረበ:: ጥር 20 ቀን ፍርድ ቤቱ የአቃቤ ሕግ ያቀረበውን ያልተሻሻለ ክስ እንደተሻሻለ መቁጠሩን በመግለጽ ተከሳሾች የኅብረተሰቡን ደህንነት ወይም ጤና በማወክ በጸረ ሽብር ሕጉ አንቀጽ 4 መከሰሳቸውን አጸና:: የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የተጠቀሰበትን አንቀጽ በቀደመው ብይን ውድቅ በማድረጉም የተከሳሾች ጉዳይ ‹‹በጸረ ሽብር›› ሕግ ብቻ እንዲዳኝ ተወሰነ:: የእምነት ክህደት ቃላቸውን እንዲሰጡም ተቀጠረ:: ጥር 26 ቀን የዞን 9 ጦማርያንና ጋዜጠኞች በድጋሚ ፍርድ ቤት ቀረቡ:: ተከሳሾች የእምነት ክህደት ቃላቸውን ከመስጠታቸው በፊት የመሐል ዳኛው እንዲነሱላቸው አቤቱታ አቀረቡ:: ችሎቱም አቤቱታውን ሰምቶ ለመወሰን ሌላ ቀጠሮ ተሰጠ:: በጥር 27 ቀኑ ቀጠሮ የተገኙት ተከሳሾች ሁለቱ ዳኞች ተሟልተው የዳኛው ይቀየርልን አቤቱታን መስማት ስላልቻሉ በማግስቱ ለጥር 28 ተቀጠሩ:: ጥር 28 ቀን የመሐል ዳኛው ባልተገኙበት ሁለቱ ዳኞች ጉዳዩን ዓይተው ‹‹የመሐል ዳኛው በፍርድ ሂደቱ ወቅት ጣልቃ አልገቡም፤ አፋጣኝ የፍትሕ ሂደቱንም አላጓደሉም›› በማለት ውሳኔ መስጠታቸው ተገለጸ:: ይህንን ተከትሎ የመሐል ዳኛው ‹‹ምንም አንኳን በጉዳዩ ላይ ዳኞች በችሎቱ ላይ አንድቀጥል ቢፈልጉም ለእኔ ግን አንዲህ እየተባልኩ በክሱ ላይ መቆየቴ አግባብ ስለማይሆን ራሴን ከችሎቱ አግልያለሁ›› በማለት አስተያየታቸውን ሰጡ:: (ነገር ግን ችሎቱን አሁንም የሚያስችሉት እኚሁ ዳኛ ናቸው::) በተመሳሳይ ዕለት ጦማሪ አቤል ዋበላ ከማረሚያ ቤት የደረሰበትን የመብት ጥሰት (በውሻ ሰንሰለት ታስሮ መቀመጡንና በማዕከላዊ ሳለ በደረሰበት ድብደባ እንዲጠቀም የተገደደውን የጆሮ ማዳመጫ መሣሪያውን መቀማቱን) አስመልክቶ ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ አቀረበ:: ይህን አቤቱታውን በጽሑፍ እንዲያቀርብ ከፍርድ ቤት ቢነገረውም በዕለቱ የነበረው ሂደት ብዙዎችን በፍርድ ቤት ውስጥ እንባ አራጨ:: በዕለቱ የነበሩት የእስር ቤት ተጠሪ ‹‹የማውቀው ጉዳይ የለም›› በማለት የመብት ጥሰቱን ክደዋል::

የካቲት 11 2007 ዓ.ም. የ‹‹የመሐል ዳኛው ይቀየርልን›› አቤቱታውን ፍርድ ቤቱ ውድቅ ካደረገው በኂላ የዞን 9 ጦማርያና ጋዜጠኞች የካቲት 11 ቀን ለ20ኛ ጊዜ ፍርድ ቤት በመገኘት የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል:: በዕለቱ ጦማሪ በፍቃዱ ‹‹የሽብር ተግባር አልፈጸምኩም፤ ሽብር ግን ተፈጽሞብኛል›› ሲል፣ ጦማሪ ናትናኤል በበኩሉ ‹‹እዚህ አገር ፍትሕ ቢኖር ኖሮ እኔ በቆምኩበት ቦታ ላይ መቆም የሚገባቸው ከሳሾቼ ናቸው፤ ምንም ዓይነት ወንጀል አልፈጸምኩም›› የሚል ቃሉን ሰጥቷል:: ጦማሪ አጥናፍ ‹‹ምንም ዓይነት ወንጀል አልፈጸምኩም›› ያለ ሲሆን ጦማሪ አቤል በበኩሉ ‹‹የኅብረተሰቡን ደህንነት ለመጉዳት አላቀድኩም፤ ለሽብር ተግባርም አላሴርኩም ብሏል::›› የሴት እስረኞችን አያያዝ አስመልክቶ አጭር ቀጠሮ የተሰጠ ሲሆን አጠቃላይ የማስረጃ ማሰማት ሂደቱን ግን ከአንድ ወር ከ10 ቀን በኂላ በተከታታይ ለሦስት ቀን ቀጥሮታል:: የካቲት 18 ቀን የሴት እስረኞችን አያያዝ አስመልክቶ የተሰየመው ችሎቱ ጉዳዩን ለማየት በድጋሚ ቀጠሮ ሰጥቷል::

መጋቢት 21 ቀን 2007 ዓ.ም. ‹‹የሰው ምስክር›› ተብለው የቀረቡ ሰዎችን ምስክርነት መስማት ተጀመረ:: ሁሉም ምስክሮች የተከሳሾች እቃዎች ሲፈተሹ ያየን ነን በማለት የተያዙ እቃዎችን ከማየታቸው በስተቀር ያቀረቡት የተለየ የወንጀል ምስክርነት አልነበረም:: ምስክሮቹ ተከሳሾን መለየት ሲያቅታቸው የተስተዋሉ ሲሆን በመጀመሪያው ቀን 6 ሰዎች ቃላቸውን ሰጥተዋል:: የተከሳሽ ጠበቆች ‹‹ባልተካደ ነገር ላይ የፍርድ ቤቱም የተከሳሾችም ጊዜ መባከን አይገባውም እቃውም የእኛ አይደለም የሚል ቃል አልሰጠንም ስለዚህ የደረጃ ምስክሮች መስማት ይቁም›› ቢሉም ፍርድ ቤቱ ‹‹ታዛቢዎቹን መስማት መቀጠል አለበት›› በማለቱ የተገኙ እቃዎችን

# ጥበባት/ ቲያትር





ሲዘረዝሩ ከርመዋል። (መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ አርቲክሎች፣ ላፕቶፖች፣ ስልኮች እና ሲም ካርዶች የመሳሰሉት ከፍተሻ ዝርዝሩ ውስጥ የተገኙ ናቸው) መጋቢት 22 ቀን ተጨማሪ 8 ምስክሮች በተመሳሳይ ሁኔታ ቃላቸውን ሲሰጡ ውለዋል። ከነዚህ በላይ ምስክሮችን ማቅረብ ያልቻለው አቃቤ ሕግ ተጨማሪ ጊዜ በመጠየቁ ለመጋቢት 30 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ተሰጥታል። መጋቢት 30 ቀን አቃቤ ሕግ ምስክሮቼ ጠፍተውብኛል ያለ ሲሆን የሲዲ ማስረጃዎችን የያዘው ሰው በአገር ውስጥ እንደማይገኝ ገልጾ ተጨማሪ ጊዜ ይሰጠኝ የሚል ጥያቄ በማቅረቡና ጥያቄው በፍርድ ቤት በመፈቀዱ ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶ ችሎቱ ተበትናል። መጋቢት 25 ቀን ጦማሪ በፍቃዱ ኃይሉ ‹‹ይድረስ ለ‹ኢቢሲ› ጋዜጠኞች›› በሚል ርእስ የጻፈው ጽሑፍ ታትሞ ወጥቷል።

ከሚያዝያ 16 እስከ 19 ቀናት 2007 ዓ.ም. የ6ቱን ጦማርያንና የ3ቱን ጋዜጠኞች እስር አንደኛ ዓመት አስመልክቶ ‹‹ለነጻነታቸው ዋጋ የሚከፍሉትን እናወድስ›› በሚል መሪ ቃል የሁለት ቀናት ማስታወሻ ተዘጋጀ። በማስታወሻው ጦማርያኑና ጋዜጠኞቹ የደረሰባቸውን የመብት ጥሰት ዝርዝር እና የተያዙበትን ዕለት የነበረውን ድባብ ያሳየ ሲሆን ከ3 ሺህ በላይ ሰዎች በኩነቱ ላይ ተሳታፊ ሆነዋል። በዚሁ የማስታወሻ ዝግጅት ላይ የዞን 9 ጦማርያንና ጋዜጠኞች የላኩት የአንደኛ ዓመት ማስታወሻም ተስተናግዷል።

ግንቦት 2 ቀን 2007 ዓ.ም. በዞን 9 ወዳጆች አማካኝነት የተዘጋጀው ሁለተኛው የቤተሰቦቻቸውን ሸክም መጋራት የሚለው የአንድ ሳምንት ዘመቻ ለሁለተኛ ጊዜ ተካሄዷል። ከግንቦት 19-21 በነዚህ ቀናት በዋለው ችሎት ላይ ከፍተኛ መወዛገብ ያሳየው አቃቤ ሕግ ሲዲዎቹን እንደ ማስረጃ ማስመዝገብ ባለመቻሉ እና ምስክሮችንም ማቅረብ ስላልቻለ ሲዲዎቹ ከማስረጃ ላይ እንዲወገዱ እንዲሁም ተጨማሪ ምስክሮችን ለማቅረብም የተወሰነው ጊዜ በቂ ሆኖ አልተጠቀመበትም በሚል ምክንያት ተጨማሪ ዕድል እንዳይሰጠው ተወስኗል።

አቃቤ ሕግ አንደኛ ተከሳሽ ሶልያና ሽመልስ ላይ አለኝ ያለውን የሲዲ ማስረጃ አስመልክቶ ሌሎች ተከሳሾች ማየት አለባቸው ወይስ ፍርድ ቤቱ በጽሕፈት ቤት ማየት አለበት የሚለውን ለመወሰን ሰኔ 8 ቀን ተቀጥሯል። በተመሳሳይ ቀን ችሎት ውስጥ አቤል ዋበላ ከዳኞች ጋር በነበረው አለመስማማት የተነሳ የችሎት መድፈር ጥፋተኛ ተብሎ ለቅጣት ለግንቦት 25 ቀን ተቀጠረ። ግንቦት 23 ቀን ሥነ ሥርዓትየሚለው የጦማሪ አቤል ዋበላ ጽሑፍ ታትሟል። ግንቦት 25 አቤል ዋበላ በችሎት መድፈር በገደብ 4 ወር ተፈረደበት።

ሰኔ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ፍርድ ቤት የቀረቡት 9 ተከሳሾች ለብይን ለሐምሌ 13 ቀን የተቀጠሩ። በዕለቱም አንደኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበውን የሲዲ ማስረጃ በጽሕፈት ቤት ዓይተን እንደማስረጃ ቆጥረነዋል። ለሌሎች ተከሳሾም መድረስ አይገባውም በማለት ችሎቱ ወሰነ።

ሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም. ዓ.ም. ባተጠበቀ ሁኔታ ሦስቱ ጋዜጠኞች እና ሁለት የዞን9 ጦማርያን ክሳቸው ተቋርጦ ከእስር የመፈታታቸው ዜና ተሰማ። በዕለቱ ጋዜጠኛ ተስፋለም ወልደየስ፣ ጋዜጠኛ አስማማው ኃይለጊዮርጊስ እና ጦማሪ ዘላለም ክብረት ሲፈቱ በማግስቱ ጠዋት ጋዜጠኛ ኤዶም ካሳዬና ጦማሪ ማህሌት ፋንታሁን ተፈቱ። በተመሳሳይ ቀን በቀሪዎቹ አምስት ተከሳሾች ላይ ክሱ እንደሚቀጥል የመንግሥት ወዳጅ የሆነው ሬዲዮ ፋና በድ ረገጹ አሳወቀ።

ከሐምሌ 9 እስከ 11 ለሦስት ቀናት የሚቆይ ‹‹እስቲ እንነጋገር የማስረጃን ነገር›› በሚል የተዘጋጀው ዘመቻ ተካሄደ። ይህ ዘመቻ ሐሳቡ በተከሳሾች ላይ ማስረጃ ተብለው የቀረቡ ጉዳዮችን ለአደባባይ ማብቃትና ቀሪ አራት ታሳሪዎች የሚከላከሉት ምንም ነገር እንደሌለ ለማሳወቅ የታለመ ነበር። ሐምሌ 10 ቀን ጦማሪ በፍቃዱ ቁዘማ፣ ከአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በፊት እና ጦማሪ ናትናኤል የዕለት ተዕለት ጥያቄዎቻችን ብይናቸውን አስመልክቶ የጻፋቸው ጽሑፎች ታተሙ።

ሐምሌ 13 ቀን ፍርድ ቤቱ የአንድ ምስክር ቃል ተገልብጦ አልደረሰኝም በማለት ብይኑን መሥራት አለመቻሉን ገልጾ ጽሑፉ መገልበጡን ለማረጋገጥ ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጠ። ሐምሌ 22 ቀን የተከሳሾች ጽሑፍ ተገልብጦ ማለቁን አረጋግጫለሁ ያለው ፍርድ ቤቱ ከጽሕፈት ቤት በማስቻል በድጋሚ ለጳጉሜ 2 ቀን ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጠ። ሐምሌ 25 ቀን ጥቂት ስለማዕከላዊ የሚል ጽሑፍ ታተመ። በዓመቱ የመጨረሻ ሳምንት የመጨረሻ የአስር ሳምንታቸው ይሆናል ተብሎ ተስፋ ቢደረግም ፍርድ ቤቱ ዳኞች አልተሟሉም በሚል ሌላ ሰበብ ሁለተኛውን እንቁጣጣሻቸውን በእስር እንደሚያሳልፉ ያረጋገጠውን የ31 ቀን እንዲቀርቡ በማዘዝ ለመስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም 37ኛውን ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል።

ትሑት ጥላሁን

## የሕፃናትና ወጣቶች ቲያትር ቤት ያለህ!

ተደጋግሞ <<ባህላችንና ዕሴቶቻችን ጠብቀን ለልጆቻችን እናስተላልፋ>> እየተባለ የሚነገር ቢሆንም የኢትዮጵያን ታሪክና ዕሴቶች መሠረት አድርገው የተዘጋጁ በቂ የሕፃናት መጻሕፍትን ማዘጋጀትና ማቅረብ አልተቻለም። ልጆቻችንን የሚያስተምሩና የሚያንጹ አገራዊ ፊልሞችና ቲያትሮች እየተዘጋጁ እንዳልሆነም ግልጽ ነው። የቤት ሥራችንን ሳንሠራ <<ልጆቻችን የምዕራባውያን ባህል ሰለባ ሆኑ>> እያልን መጮሃችን መሠረት የሌለው ከንቱ ጩኸት ነው። ባልደረባችን ትሑት ጥላሁን ባለሙያ አነጋግራ የሚከተለውን ጽሑፍ አዘጋጅታለች።

በዓለም ዙሪያ የሕፃናትና ወጣቶች ትያትር በየዓመቱ መጋቢት 20 ቀን (አ.አ.) ተከብሮ ይውላል። ምናልባትም አስቂኝ ልብስ የለበሱ ተዋንያን መድረክ ላይ ሲዘፍኑ፣ ሲደንሱና ሲሯሯጡ የሚታዩበትን ትያትር ዓመታዊ ቀን ሰይሞ ማክበር አስፈላጊ መስሎ ላይታየን ይችላል። ነገር ግን የሕፃናት ትያትር እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ የትያትር ዘርፍ ነው። የምንመለከታቸው ወይም የምናነባቸው የጥበብ ሥራዎች ለነገሮች ያለንን ምልከታ እንደሚቀይሩት ሁሉ ልጆችም የሚያነቧቸው መጻሕፍት፣ የሚመለከቷቸው ፊልሞችና ትያትሮች ተጽዕኖ ያደርጉባቸዋል። በመሆኑም ልጆች በትያትርና በፊልም ያዩትን፣ ከመጻሐፍት ያነበቡትን ወዘተ. ተግባራዊ ያደርጋሉ። ስለዚህም ለልጆች የሚዘጋጁ ትያትሮች አስምሮታዊ ይዘት አላቸው። ትያትር የሚመለከቱ ሕፃናት ከማይመለከቱት ይልቅ አእምሮአቸው የበሰለና የፈጠራ ችሎታቸው የዳበረ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ።

በሥነ ልቦና መስክ የሰው ልጅ አዕምሮ የቀኝና የግራ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። የቀኙ የአዕምሯችንን ክፍል የምንጠቀመው የምርመራ ወይም ትንተና እና ተገቢ ወይም አመክኗዊ አስተሳሰብ ላይ ሲሆን የግራው የአዕምሯችን ክፍል የሚጠቅመን ደግሞ ስሜትን ለመረዳት ወይም ለመገንዘብና ለፈጠራ ችሎታ ነው። ይህ የአዕምሯችንን ክፍል በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚለው አንድ ሰው በፈጠራ ሥራዎች ላይ ሲሳተፍ ነው። የሥነ ልቦና ባለሙያዎች <<አዕምሯችን ብቃት ያለው እንዲሆን ሁለቱም ክፍሎች እኩል መዳበርና በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል>> ይላሉ። ሕፃናት በትምህርት ቤት በሚሰጧቸዉ የሒሳብ፣ ቋንቋ፣ ሳይንስና ሌሎች ትምህርቶች አማካኝነት የቀኙ የአዕምሯቸው ክፍል ይዳብራል። የግራው የአዕምሯቸው ክፍል ከቀኙ ጋር አብሮ እንዲያድግ በትምህርት ቤት ከሚያገኙት የሥነ ጥበባት ትምህርት በተጨማሪ ለፈጠራ ሥራዎች ቅርብ መሆን ይኖርባቸዋል። የፈጠራ ሥራዎችና ባህላዊ ትውፊቶች ላይ የሚሠራው <<The Right Brain Initiative>> የተባለ ድርጅት እ.ኤ.አ መስከረም 2014 ዓ.ም. ባወጣው ጥናት ላይ እንዳመለከተው የተለያዩ የጥበብ ትምህርቶችን በትምህርት ሥርዓት ውስጥ በማካተት ብቻ የተማሪዎች የማበብና የሒሳብ ትምህርት ውጤት በ2.5 በመቶ መጨመር እንደተቻለ ገልጿል።

ሕፃናት በባህሪያቸው ስዕል፣ ሙዚቃ፣ ፊልምና ትያትር ይወዳሉ ተፈጥሯዊየሆነየትወናናየፈጠራችሎታምአላቸው።መቼምየ<<እቃ እቃ>> እናት ወይም አባት ሆኖ ልጆቹን ያልቀጣ፣ <<ሙሽራ>> ያልሆነች፣ የእቃ እቃ አስተማሪ ሆኖ ያላለፈ፣ <<የቅጠል እንጀራ>> ያልጋገረች፣ በኮባ የተሠራ ጠመንጃ ያልተኮሰ ልጅ የለም። ተውኔት የፈጠራ ውጤት እንደመሆኑ ልጆችን ሐሳበ ሰፊ ከማድረጉም በላይ ነገሮችን በትኩረት የማየት ችሎታቸውን ያሳድጋል። በአሁኑ ጊዜ ልጆች በአብዛኛው ፊልሞች ላይ በሰከንዶች የሚቀያየሩ ምስሎችን ስለሚመለከቱ ከፈጣን ለውጥ ጋር ተላምደዋል፤ እንዲሁም ቃለ ተውኔቱን በትኩረት አያዳምጡም። ለረጅም ጊዜ ጨለማ ክፍል ውስጥ አንድ ወንበር ላይ ተቀምጠው ከአሁን አሁን ምን ይፈጠራል ብለው ትያትርን በትኩረት መመልከታቸው አዕምሯቸውን በብዙ መልኩ ያሰፋል ይላሉ ባለሙያዎች።

ለሕፃናት የሚዘጋጁ ትያትሮች በድርጊት የተሞሉና አስተምሮታዊ ይዘት ያላቸው ናቸው። ትያትሮቹ በድርጊት የተሞሉና ፈጣን እንቅስቃሴ ያለባቸው መሆናቸው ልጆቹ በአትኩሮት እንዲከታተሉ ያደርጋቸዋል። የሕፃናት እና ወጣቶች ትያትር የኪነ ጥበብ ልማት ሲኒዬር ኦፊሰር የሆኑት አቶ እስጢፋኖስ ከበደ የሕፃናት ትያትርን <<ልጆች የሚቀረጹበትና ሥነ ልቦናዊ ሕክምና የሚሰጥ ነው>> ሲሉ ይገልጹታል። አቶ እስጢፋኖስ <<ትያትር የሚመለከቱ ልጆች በሥነ ምግባር የታነጹ፣ ዓላማቸውን የሚያውቁ፣ በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ታላላቆቻቸዉን የሚያከብሩና አገራቸውን የሚወዱ ይሆናሉ>> ሲሉ ያክላሉ።

የሕፃናት ትያትር እያዝናና የሚያስተምር እንደመሆኑ ልጆች የሚወዷቸውን አንደ እንስሳት፣ ጣፋጭ ምግቦች፣ አስማትና ልዩ ፍጡራንን በገጸ ባህሪነት ይይዛል። ሕፃናቱ የእድሜ እኩዮቻቸውን መድረክ ላይ ሲዘፍኑ፣ ሲተውኑና ሲደንሱ የማየት ዕድልም ይኖራቸዋል። የሕፃናት ትያትር ለአንድ እና አንድ ምክንያት ሲባል በጥሩ ሁኔታ ተጽፎ መዘጋጀት ይኖርበታል። ልጆች ከአዋቂ ተመልካች ይልቅ የሚፈታተኑን ተመልካቾቸ ናቸው። የሚያዩትን ነገር ካልወደዱት በይሉኝታ ዝም ብለው አይቀመጡም። ንጹህና ማስመሰል የማያውቁ በመሆናቸው ስሜታቸውን የሚይዝ ተውኔት ይዘን ካልቀረብን የሚቁነጠነጡ፣ እርስ በእርሳቸው ጮክ ብለው የሚነጋገሩ እና በተደጋጋሚ ወደ መጸዳጃ ቤት የሚሄዱ ልጆች ይበዛሉ።

የሕፃናት ትያትር ህፃናቱን ለማዝናናት እና ለማስተማር ከመዋሉም ባሻገር ወላጆችም ይማሩበት ዘንድ ጥቅም ላይ ይውላል። የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት አቶ አቦነህ አሻግሬ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2012 ዓ.ም. <<Children’s Theatre in Ethiopia>> በሚል ርእስ በጻፉት ጸሑፍ ላይ እ.ኤ.አ ከ1994 እስከ 1997 ዓ.ም. በዩኒሴፍ፣ ዩኔስኮና <<RADABARNA>> በተባለ ድርጅት ድጋፍ በሕፃናት እና ወጣቶች ትያትር ቤት ሰባት አስተማሪ ትያትሮች መቅረባቸውን ገልጸዋል። ጉንቀኣል፣ ደወል፣ ባለጠመንጃው፣ የተስፋ ቀን፣ እርገጤ፣ ራጂ እና የገላ ትሩፋት የተባሉት እነዚህ ተውኔቶች ወላጆችን ስለ ጎጂ ባህላዊ ልማዶች፣ ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ እና ስለሕፃናት እንክብካቤ ለማስተማር ታቅደው የተዘጋጁ ነበሩ።

ሕፃናቱ ትያትርን ከመመልከት ባሻገር በትወና፣ በሙዚቃና በውዝዋዜ መሳተፋቸው በተለያየ ዘርፍ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ያግዛቸዋል። አንድን ድርሰት እንብበው ቃለ ተውኔቱን ማጥናታቸው የማንበብና የማታወስ ችሎታቸውን ለማሳግ በእጅጉ ያግዛል። ከትያትሩ አዘጋጆች ጋር በጋራ መሥራታቸውም የማዳመጥ ችሎታቸውን ያሳድገዋል። መድረክ ላይ ሲተውኑም በራስ የመተማመን መንፈስን ያዳብራሉ። ትያትሩ በዝግጅት ላይ ባለበት ወቅትም ሆነ ለተመልካች መቅረብ ከጀመረ በኋላ በትያትሩ ውስጥ የሚሳተፉ ልጆች በብዙ መልኩ ያድጉበታል። በተጨማሪም በጥበቡ ዘርፍ ለመቀጠል ፍላጎቱና ስጦታው ላላቸው ልጆች መነሻ ይሆናቸዋል።

የትያትር ጥበብ በአገራችን ከዘጠና ዓመታት በላይ እድሜ ቢኖረውም የህፃናት እና ወጣቶች ትያትር እስከተቋቋመበት 1981 ዓ.ም. ጊዜ ድረስ ለሕፃናት ተብሎ የተዘጋጀ ትያትር ቤት አልነበረም። ትያትር ቤቱ የዝናብዋ እመቤት የሚል ትያትር በማቅረብ <<ሀ>> ብሎ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እንደ ሆድ አምላኩ፣ አባ ጉጉ፣ ተንኮሉ፣ ብልጣብልጥ፣ የቀበሮ ባህታዊና የመሳሰሉ ተወዳጅ ትያትሮችን ለታዳሚው ሲያቀርብ ቆይቷል። ከአራት ኪሎ ወደ ቀበና መገናኛ በሚወስደው መንገድ ላይ የሚገኘው ትያትር ቤት ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ለልጆችና ልጆቻቸውን ይዘው ለሚታደሙ ወላጆች ምርጥ ምርጥ ትያትሮችን፣ ሙዚቃና ውዝዋዜን ሲያቀርብ ቆይቷል።

በሕፃናትና ወጣቶች ትያትር ልጆች በሙዚቃ፣ በውዝዋዜ፣ በመድረክ መሪነትና አልፎ አልፎም በትወና ይሳተፋሉ። በሚዘጋጁት ትያትሮች ላይ በዋና ገጸ ባህሪነት የሚሳተፉት አዋቂዎች ሲሆኑ ሕፃናቱ ሥልጠና ተሰጥቷቸው በረዳት ተዋናይነት ይሳተፋሉ። በቀጣዩ ዓመት ትያትር ቤቱ ለሕፃናቱ የትወና ሥልጠና ለመስጠትና ሕፃናቱን በትወና ለማሳተፍ ዕቅድ ይዟል።

ምርጥ ምርጡን ለሕፃናት እንደመሆኑ በተለይም በልጆች መዝናኛ ላይ የሚሠሩ ድርጅቶች ለልጆች ሁሌም የተመረጡና የተሻሉ ነገሮችን ለማቅረብ ይሞክራሉ። ወላጆችም በተቻላቸውና አቅማቸው በፈቀደላቸው ሁሉ ለልጆቻቸው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ያሟላሉ። ምን ያክሉ ወላጅ ነው ልጆቹን መጽሐፍ እንዲያነቡ፣ የሕፃናት ፊልምና ትያትር እንዲያዩ የሚያበረታታው የሚለውን ጥያቄ ወላጆች ራሳቸውን ይጠይቁ ዘንድ እንተወው።

ወደ ትያትር ቤት ልጆቻውን ይዘው ለሚሄዱት ወላጆችም ምቹ የሆነና በቂ መቀመጫ ያለው የትያትር አዳራሽ የለም። በከተማችን ያለው ብቸኛ የሕፃናት ትያትር ቤት የሕፃናትና ወጣቶች ትያትር ሁለት መቶ ሀምሳ ሰዎችን ብቻ የማተናገድ አቅም ያለው ነው። ትያትር ለመመልከት በታላቅ ጉጉትና በናፍቆት ቅዳሜ እና እሑድን ሲጠብቁ የቆዩ ልጆች በቦታ ጥበት ምክንያት አገልግሎት ማግኘት አለመቻላቸው የሚያሳዝን ነገር ነው። በትያትር ቤቱ ሙዚቃና ውዝዋዜ ለሚለማመዱ ልጆች በቂና ምቹ የመለማመጃ ቦታ አለመኖሩም ሌላው ችግር ነው።

ይህ የቦታ ጥበት ችግር ግን በቅርቡ እንደሚቀረፍ የትያትር ቤቱ የኪነ ጥበብ ልማት ሲኒዬር ኦፊሰር ከሆኑት አቶ እስጢፋኖስ ከበደ ሰምተናል። ከመንግሥት በተመደበ በጀት ከኤግዝቢሽን ማዕከል ጀርባ ባለ ዐሥራ አንድ ፎቅ ሁለገብ ማዕከል በግንባታ ላይ መሆኑንና በ2008 ዓ.ም. መጨረሻ ወይም በ2009 ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ ግንባታው ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ይጀምራል ተብሎ እንደሚጠበቅም ነግረውናል። ይህ ማዕከል ከአንድ ሺ ሁለት መቶ በላይ ተመልካችን የመያዝ አቅም ያለው የትያትር አዳራሽ ሲኖረው ለትያትር ቤቱ ተዋንያንና በትያትር ቤቱ ሥር ለሚሠሩ ልጆች በቂ የሆነ የመለማመጃ ስፍራ እንደሚኖረውም ተገልጿል።

እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም ከሕዝቡ ቁጥር አንጻር ሲመዘን ግን ጨርሶ በቂ አይደለም። በሚያሳዝን ሁኔታ በአገሪቱ ያለው የሕፃናት ትያትር ቤት አንድ ብቻ ነው። ትያትር ቤቱ በሳምንት ሁለት ቀን የሚያሳየው ትያትር በአዲስ አበባ ላለው ተመልካችም የሚበቃ አይደለም። በክፍለ አገር ያሉ ሕፃናት ትያትር መመልከት የሚችሉበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም። ትያትር የነገ አገር ተረካቢ ለሆኑት ሕፃናት ሥነ ልቦናዊ እድገት ከሚጫወተው ትልቅ ሚና አንጻር ለእድገቱና በአገር ዐቀፍ ደረጃ ለመስፋፋቱ ይበልጥ ሊሠራ ይገባል። ልጆቻችን እውነትም የነገ ፍሬዎች ሊሆኑ የሚችሉት ከወዲሁ ተኮትኩተው ሲያድጉ ነውና ለዚህ ዘርፍ ልዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

# ትውስታ

# “ደቼ” እና ትዝታዋ

ሙሉቀን ተስፋው



ጅማ ዩኒቨርሲቲ እያለን አንዲት ‹‹ዶቼ›› ስለምትባል ፍጡር የምንሰማው ‹‹ትውፊት›› ነበር:: እውነት ይሁን ውሸት በጊዜው ማናችንም ማረጋገጥ አንችልም:: ሆኖም ከልባችን የሚነገረንን እንደእውነት እንቀበለዋለን:: ‹‹ሲኔሮች›› ሲለቁ ለተከታዮች ትውፊቱን ያስተላልፋሉ:: ከዚህ በታች ያለው ታሪክ በትውፊቱ መሠረት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው::

ሰኞና አርብ በዩኒቨርሲቲዉ ፖስታ ቤት በኩል ደብዳቤ የመጣለቸው ተማሪዎች ስማቸውን ፍለጋ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ይጋፋሉ:: የፖስታ ቤት ሠራተኛዋ ደብዳቤ ስትለጥፍ በአካባቢው የነበረ ተማሪ ቀድሞ የማንበብ ዕድል ስለሚኖረዉ ዕድለኛ ሆኖ ከመጣለት ተራ ቁጥሩን ይይዝና ደብዳቤውን ለማውጣት ይሮጣል፤ ካልመጣለትም ቁርጡን ያውቃል:: ዘግይቶ የደረሰ ተማሪ ግን ወይ መጋፋት አለበት አሊያ ደግሞ ጋብ የሚልበትን ሰዓት መጠበቅ ግድ ይለዋል:: አንድም ቀን ደብዳቤ መጥቶላቸው የማያውቁ ልጆች ሳይቀሩ በተሰፋ አብረው ይጋፋሉ:: ደብዳቤ የሚልክላቸው ሰው እንደሌለ እያወቁም ቢሆን ስማቸውን ፍለጋ ይደክማሉ:: ዕድለኛ ሆነን ደብዳቤ ከደረሰን ከምናጠናው ትምህርት (ሃንዳውት) ጋር አብረን ይዘነው እንዞራለን:: አዲስ ተማሪ መሆን ፈተናው ብዙ ነው:: ናፍቆቱም ከብዙ ነገር ጋር ነው:: የማይናፍቅ ነገር የለም:: ይህ እኔን ጨምሮ አዲስ ተማሪዎች የምንሰቃይት ነው:: የሥነ ልቦና ባለሙያዎቹ አዲስ ተማሪዎች በጭንቀት - General Anxiety Disorder (GAD) የሚጠቁበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው ይላሉ::

አገሬ ትቻት የመጣኋት ፍቅሬ ናፍቆት ያሰቃየኛል:: የፍቅሬ ቤተሰቦች ስልክ የላቸውም:: ሞባይልማ ጨርሶ የሚታሠብ አልነበረም:: እንዲያውም ከመጣሁባት ከተማ የተንቀሳቃሽ ስልክ አገልግሎት መስጠት አልጀመረም:: በጎረቤታቸው በኩል በቀጠሮ ከሳምንት አንድ ቀንም ካገኘኋት ለኔ ስንቅ ነበር:: የገና አካባቢ የደረሰኝን የእናቴን ደብዳቤ ደጋግሞ ማንበብ ‹‹እናት›› ካፌ ከመመገብ በላይ ያጠግበኝ ነበር:: ኧረ ቋጥሬው ከመጣሁት ዳቦ-ቆሎና በሶ በላይ ያረካኝም ነበር! በወር አንዴ ከፍቅሬ ደብዳቤ ይደርሰኛል:: በአስቸኳይ ካልተላከ በስተቀር ጊዜ ጨርሰን የምንጽፈዉ ደብዳቤ ከወር በፊት አይደርስም:: የአገራችን የፖስታ ቤት አሠራር ከኤሊ ይዘገያል:: ጥቅምት ላይ የተላከልን ደብዳቤ ገና ካለፈ በኋላ ሊደርስ ይችላል:: በሚያዚያ አካባቢ የተላከ ደብዳቤ በሐምሌ ከዩኒቨርሲቲው እስከምንወጣ ድረስ እጃችን ላይገባ ይችላል:: የሚገርመው ደግሞ አንድ ድብዳቤ ለመጻፍ የምናባክነው ጊዜና ጉልበት አንድ ጥናታዊ ጽሑፍ (ፔፐር) ከመሥራት ይከብዳል:: በደብዳቤ አጻጻፍ የላቀ ክህሎት ያላቸው ልጆች እንደ አማካሪ ሆነው የማያስፈልጉ ሐሳቦችን በመሰረዝና በመደለዝ የተሻለ ጦማር እንዲወጣዉ ያደርጋሉ:: ጥሩ ደብዳቤ ለማዘጋጀት አንድ ሣምንትም አንድ ወርም ሊጠይቅ ይችላል:: ፌስቡክ የለ፤ ኢሜል የለ፤ ሞባይል የለ፤ ኢንተርኔት የለ…::

ከፍቅሬ የደረሰኝን ደብዳቤ ይዤ ‹‹ስቴስ›› ሄድኩ:: በማግስቱ የማጠቃለያ ፈተና ይጠብቀኛል:: ይሁን እንጅ ከሃንዳውቱ ይልቅ ደጋግሜ የቸከልኩት የፍቅሬን ደብዳቤ ሲሆን ደጋግሜ ያየሁት አብሮ የደረሰኝን የፍቅሬን ፎቶ ግራፍ ነበር:: ደብዳቤውን ሳነብ ፍቅሬን ለማስመሰል እሞክራለሁ:: ስትጽፈው የነበረችበትን ሙድ አስባለሁ:: በሐሳብ አቅፋታለሁ:: ፎቶዋን ደጋግሜ እስማለሁ:: የምትሰማኝ ይመስል አናግራታለሁ:: አሁን በምን ሁኔታ ላይ እንዳለች አስባታለሁ:: ‹‹ይኼን ጊዜ እኮ እሷም እንደኔ በናፍቆት እየተሰቃየሽ ይሆናል!›› እላለሁ:: ‹‹ውዴ በጣም ናፍቀሽኛል፤ ስትሸኝኝ ‹ዓመት ዕለት ነው› ብለሽኝም አልነበር! አይዞሽ ከአራት ወራት ያልበለጠ ጊዜ ነው የቀረን›› እንደምትሰማኝ ሁሉ በምናብ አወራለሁ::

በማጠናበት ክፍል አንዲት ፍልቅልቅ ቆንጆ እየሳቀች ወደኔ መጣች:: አዎ- አውቃታለሁ፤ የኔዋ ናት፤ ውዴ:: በሕልም ይሁን በእውን እየሆነ ያለው ግራ ገባኝ:: በእኩለ ሌሊት ያውም ከሺህ በላይ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጣ ጂማ መገኘቷ ምን ሊሆን ይችላል? ጅማ ፈረንጅ አራዳ አሊያም መርካቶ ቢሆን ብዙም ላይገርም ይችላል፤ ግን ከጂማም በእኩለ ሌሊት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ገብታለች፤ ከዚያም አልፋ ከማጠናበት ስቴስ ድረስ መጥታለች!! ሁሉ ነገር ዞረብኝ! ለምንስ አይዞርብኝ?

**በሐሳቤ ‹‹አሃ ያች በእኔ ፍቅር ተመስላ የመጣችብኝ ደቼ ናት ማለት ነው?›› እራሴን ጠየቅኩ። ከጠበል መልስ ወደ ግቢ ስንገባ አንደኛው ‹‹ደብዳቤ መጥቶልሃል ውሰድ!›› ብሎ ወደ ፖስታ ቤት አዘገምን። የላኪዉ አድራሻ ላይ የፍቅሬ ስም አለበት።**

ግራ ተጋብቼ ሳለ ‹‹አልናፈኩህም የኔ ውድ?›› እየሳቀች ጠየቀችኝ::

‹‹ቆይ እንዴት መጣሽ? እንዴት ገባሽ? መቼ መጣሽ?›› የመጣልኝን ጠየቅኋት::

‹‹ናፈቅሽኛ! ይልቅስ ተነስ ሳመኝ! እኔ አንተን ብየ ይህን ያክል መሰዋዕትነት እየከፈልኩ ዝም ትላለህ? ምን ያክል ናፍቀሽኝ እንደሆነ ማን በነገረልኝ?›› ልትስመኝ እጇን ዘረጋች::

ለመነሳት አቅም አጣሁ:: እጄን ዘረጋሁ:: እጄን ጨብጣ እንድነሳ ሳበችኝ:: ምን እየተከናወነ እንደሆነ እርግጠኛ አልነበርኩም:: ፍቅሬ ናፍቃኛለች:: ሙሉ ጊዜየን ስለእሷ በማሰብ አጥፍቻለሁ:: ያን ያክል ጊዜ ሃንዳውቴ ላይ ብቆይ ኖሮ የነገው ፈተና ‹ኤ› እንደሚሰቀል ምንም አልጠራጠርም:: ግን አልሆነም::

ኧረ የምናባቱ ‹ኤ› ነው:: ፍቅሬን በዚህ ሰዓት ማገኘት ከ‹ኤ› በላይ ነው:: ውዴን አቀፍኳት:: የደስታ እምባ በጉንጮቼ ላይ ሲፈስ ተሰማኝ:: የናፈቀኝን ከንፈሯን ጎረስኩት:: ጎረሰችኝ:: እኩለ ሌሊት አልፏል:: ማንም ሰው በዚያ ክፍል ውስጥ አልነበረም:: ቢኖርም ግድ አልነበረኝም:: በዚህ ሰዓት እንደኔ ተዓምር የተሠራለት ማንም ሰው በምድር ላይ አይኖርም::

‹‹በቃህ አሁን ከተማ አልጋ ይዣለሁ፤ ለግቢው ፖሊሶች እንደምንወጣ ስላስፈቀድኳቸው መውጣት እንችላለን:: ሆስፒታል በር የሚጠብቀን ታክሲ አለ፤ እንፍጠን›› አለችኝ እንድለቃት እየታገለችኝ:: ሃንዳውቴና እርሷ የላከችልኝን ደብዳቤ በፍጥነት መሸካከፍ ጀመርኩ:: እስክርቢቶየ ወደቀ:: ተንከባልሎ ወደ ፍቅሬ እግር ሄደ:: ከእግሯ ሥር የወደቀውን እስክርቢቶ ሣላነሳው በድንጋጤ ጮህኩ:: በሳቅ ፍርስ ስትልብኝ እኔ እየሮጥኩ ነበር:: ምን እያልኩ እንደምጮህ እግዜር ይወቀው:: ሦስቱንም ፎቅ በምን ያክል ፍጥነት እንደወረድኩት አላውቅም:: በግተራ አካባቢ ስደርስ ፖሊሶች ደረሱልኝ::

‹‹ተረጋጋና የሆንከውን አስረዳን?›› የፖሊስ አዛገፍ ይጠይቀኛል:: እየተንቀጠቀጥኩ ‹‹ከዚያ … ከዚያ … ስቴስ ሳነብ …›› መጨረስ አልቻልኩም::

‹‹ቀጥል ቀጥል ስቴስ ምን ገጠመህ?›› አንደኛው ፖሊስ ጠየቀኝ::

‹‹የከብት ሸኮና ያላት ል…ጅ መጣችብኝ›› ስላቸዉ

ሦስቱም ፖሊሶች በአንድ ድምጽ እግራቸውን እያነሱ ‹‹ልክ እንደዚህ ነው?›› ብለው ተመሳሳይ የከብት እግር አሳዩኝ::

ከዚያ በኋላ ምን እንደተፈጠረ አላውቅም:: ስነቃ ነጭ ልብስ የለበሱ ሰዎች ከበውኛል:: መቼና እንዴት እንደመጣሁ ትዝ አይለኝም::

‹‹ማን ከዚህ አመጣኝ? የት ነው ያለሁት?›› ወደ ታች የሚመለከተኝን ሐኪም ጠየቅኩት:: ስሜን ጠርቶ ትንሽ አሞኝ እንደነበር፣ ያለሁትም ሆስፒታል መሆኑን በእርጋታ አስረዳኝ::

‹‹እግርህን አሳየኝ? ቶሎ በል እግርህን አሳየኝ?›› የሚናገረኝን ሐኪም ጮህኩበት::

‹‹እ… የተሻለዉ መስሎኝ ነበር! I think he is in state of hallucination and delusion still now. He needs advanced psychiatric treatment. We should refer him to Emannuel Hospital›› ጓደኛውን ሀኪም በሐሳቡ ላይ ያለውን አስተያየት እንዲሰጠዉ ይመለከተዋል::

‹‹ለአንድ ሣምንት የከበት እግር፣ ሸኮና፣ ፖሊስ፣ ፍቅሬ … እያለ ሲለፈልፍ ነው የሰነበተው:: ከፍተኛ የአዕምሮ ሕክምና የሚያስፈልገው ይመስለኛል›› ሌላዉ ሰዉ ተቀበለው::

‹‹እግራችሁን አሳዩኝ?›› ላንቃዬ እስኪሰነጠቅ እጮካለሁ::

የዶርምና የክፍል ጓደኞቼ ከተኛሁበት ክፍል እየመጡ ከንፈራቸውን ይመጣሉ::

‹‹ስለ ኪዳነ ምህረት ብላቸዉ ከዚህ ከሰይጣናት ዓለም ዉሰዱኝ? ቆይ ግን መምህሬ ሰይጣን ሲያማትቡበት 40 ክንድ ይርቃል ብለውም አይደል? ይኸው ‹በስመ አብ ወወለድ ወመንፈስ ቅዱስ…› በቃ በቃ እናንተ ጓደኞቼ ናችሁ:: ሰይጣን ብትሆኑ እኮ ከፊቴ አትቆሙም ነበር:: እኔ ደግሞ እንደነዚያ ሾኮና ያላቸዉ ሰይጣኖች መስላችሁኝ ነበር›› እለፈልፋለሁ:: ጓደኞቼ እንደ እብድ ቆጥረው ከንፈራቸውን ደጋግመው ይመጣሉ::

….

ቀዝቃዛ ጠብል እየፈሰሰብኝ ነው:: ሁለት ወጠምሾች ሁለቱንም እጆቼን ፈጥርቀው ይዘዋቸዋል:: ቄሴ በመስቀላቸዉ እየደበደቡ ‹‹ልቀቅ? ማነህ?›› ይላሉ:: ‹‹ወይኔ በቃ አብጃለሁ ማለት ነው! ለካ እብደት ማለት ይህ ነው! ለካ አብጃለሁ! አይ እኔ እብዱ!›› ጠበሉ እየፈሰሰብኝ አለቅሳለሁ::

‹‹የሚገርምዎት አባ ትናንት በሌሊት ሁሉንም ልብሱን አጥቦት አደረ:: ጠዋት ‹ማነው የኔን ልብስ አጥቦ ውጭ ያሰጣዉ? እስኪ አሁን ምን ልልበስ?› ብሎ አይቆጣም መሰልዎት:: ይባስ ብሎ ዛሬ ደግሞ ዶርሜ ውስጥ ነው የምተኛ ብሎ ሽንት ቤት ሲጮህ አደረ›› የዶርም ጓደኞቼ ለቄሱ የሚያቀርቡት ምስክርነት::

‹‹ይሻለዋል፤ ለኪዳነ ምህረት ምን ይሳናታል!›› ቄሱ ያጽናናሉ:: ‹‹ሲጀምረው ማን አብሮት ነበር?›› ቄሱ ማብራሪያ ፍለጋ ጓደኞቼን ያያሉ::

‹‹ከእኛ ግቢ ያለችው ዶቼ ዘንድሮስ ብሶባታል:: ለዩንቨርሲቲው ግንባታ ትልልቆቹን ዋርካዎች ከቆረጡባት በኋላ ነው አሉ እንደዚህ ብዙ ተማሪ ላይ የምትሰፍር:: ባለፈዉ ዓመት አንድ የሥራ አመራር ተማሪ ቴክኖ ስቴስ ሲያነብ ጠፋ:: ተፈልጎ ተፈልጎ ዩኒቨርሲቲውም ወላጆቹም ተስፋ ቆርጠው ሳለ ዘንድሮ ከዚያ ሲያጠናበት ከነበረው ክፍል ሃንዳዉቱን ይዞ ተገኘ:: ‹ፈተና በ8፡00 ነበርን እኮ የእኛ ክፍል ተማሪዎች የት ቀሩ?› እያለ ተማሪ ይጠይቃል:: የእርሱ ጓደኞች በሙሉ በዚያው ዓመት ተመርቀው ስለነበር አንድም የሚያውቀው ሰው ሲያጣ ወደ ዶርሙ ሄደ:: ሌላ ተማሪ ተመድቦበት አገኘ:: ‹የእኔ አልጋ ነው የእኔ አልጋ ነው› በሚል ጠብ ፕሮክተር (ሞግዚቶች ጋር) ከሰሰ:: በኋላ የዩኒቨርሲቲው አመራር ችግሩን ተረድቶ ከአንድ ዓመት በኋላ ተመለስ ብሎ ወደቤተሰቡ ላከዉ›› ጓደኛየ የተጠየቀው ስለኔ ቢሆንም ሌላ የደቼን ታሪክ ይዘባርቃል::

በሐሳቤ ‹‹አሃ ያች በእኔ ፍቅር ተመስላ የመጣችብኝ ደቼ ናት ማለት ነው?›› እራሴን ጠየቅኩ:: ከጠበል መልስ ወደ ግቢ ስንገባ አንደኛው ‹‹ደብዳቤ መጥቶልሃል ውሰድ!›› ብሎ ወደ ፖስታ ቤት አዘገምን:: የላኪዉ አድራሻ ላይ የፍቅሬ ስም አለበት::

አሰብኩ፤ ስቴስ ስሄድ፣ የሷን ደብዳቤ ሳነብ፣ በሸኮና እግሯ ስትመጣብኝ፣ ሁሉ ነገር በምናቤ ሳልኩት:: ከዚያ በኋላ ፍቅሬና ዶቼ አንድ ሆኑብኝ:: ፍቅረ ቢጽ ወደ ፍቅረ ዶቼ ሲቀየር አየሁት:: ዶቼን የሳምኩበትን ከንፈር አስታወስኩት:: ዳሰስኩት፤ ይሻክራል:: አከኩት፤ ደማ:: ጓደኞቼ እጀን ያዙት:: ደብዳቤውን ቀደድኩት:: የፍቅሬ ፎቶ ውስጥ ነበር:: አብሮ ተቀደደ:: ዶቼን የጎደኋት ያክል ተሰማኝ:: የቆሻሻው መውረጃ ቱቦ ውስጥ ጨመርኩት:: ከዚያን ቀን ጀምሮ ፍቅሬና ዶቼ አንድ ናቸው:: የፖስታ ቤት ማስታወቂያ መለጠፊያ ቦርድ ስሄድ ከዶቼ የመጣልኝን መልዕክት ለመቀበል የምሄድ እየመሰለኝ በዚያ ሰፈር ማለፍን ፈራሁ:: ‹‹በስመ አብ ወወለድ ወመንፈስ ቅዱስ… ሑር አንተ

## ነፃ ሃሳብ

# ጉባኤው !

መስከረም አበራ

የኢሕአዴግ ጉባኤ ከመካሄዱ ትቂት ሳምንታት ቀደም ብሎ የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች ስብሰባ ቆምንለት በሚሉት ብሔረሰብ ክልል ዋና ከተሞች ተካሂዷል፡፡ እኔ የምኖርባት ሐዋሳ ከተማም ከኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች አንዱ የሆነው የደኢሕዴን መቀመጫ በመሆኗ ይህንኑ ስብሰባ ስታካሂድ ሰንብታለች፡፡ ስብሰባው ሲካሄድ በስብሰባ አዳራሹና ባለሥልጣናቱ አረፉባቸው በተባሉት ሆቴሎች አካባቢ ያሉ ጎዳናዎች ለሲቪሉ ሕዝብ የጉዞ ዕግድ ተጥሎባቸው፣ የመለዮ ለባሹ መንጎራደጃ ብቻ ሆነው ከርመዋል፡፡ የሚገርመው በክልክል ጎዳናዎቹ ግራ ቀኝ የጀበና ቡና የሚሸጡ ወገኖች ሳይቀሩ ጉባኤው እስኪፈጸም ከዚያ አካባቢ እንዲጠፉ መደረጉ ነው፡፡ እነዚህ በቀን ገቢ ቤተሰብ የሚያስተዳድሩ ዜጎችን ጉባኤው እስኪፈጸም ምን በልተው እንዲኖሩ ታስቦ ቀጭኑ ትዕዛዝ እንደተሰጣቸው ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ ለማኛውም የተጀመረ ማለቁ አይቀርምና ጉባኤው ተፈጽሞ ተሰብሳቢዎቹ ለታላቁ የኢሕአዴግ ጉባኤ ጉዞ ወደመቀሌ ሆነ፡፡ ከአባል ድርጅቶቹ ስብሰባ እስከ ታላቁ የኢሕአዴግ የመቀሌ ጉባኤ ድረስ በዘለቀው ሂደት ትዝብት የሚያጭሩ ጉዳዮች አልጠፉም፡፡

ትዝብት አንድ፡- የዘገባው ነገር

የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች ስብሰባ ሲከናዎን የቀድሞው ኢቲቪ የአሁኑ ኢቢሲም የአባል ድርጅቶቹን ውሎ እየተከታተለ ዘግቧል፡፡ የገኘሁውን ግንባር ጉባኤ ውሎ በቀን በማታ ሲዘግብ የኖረው ኢቢሲ ትንሽ ቆየት ብለው የተደረጉትን የሰማያዊ ፓርቲንና የመድረክን ጉባኤዎች ለመዘገብ ወገቤን ማለቱ ሚዲያው የኢትዮጵያ የሚለውን ስሙን የኢሕአዴግ በሚል ግብር የቀየረ፣ ቀድሞም የሚታወቅበትን የገለልተኛነት ችግር ያባባሰ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ ሕዝብ ገንዘብ የሚሠራው ይህ የቴሌቪዥንና ሬዲዮ ድርጅት የቀድሞ ነገሥታት ዜና መዋዕል ጸሐፊዎችን ይመስል የገኘሁውን ግንባር ገድል በጎ በጎውን በማስቀደም ለማብሰር የማይደክመውን ያህል ስለተቃዋሚ ፓርቲዎች አንዳች ትንፍሽ ይል ዘንድ ከወደደ እንኳን የተቃዋሚዎቹን ገበና ለማውጣት፣ ሲነታረኩ ወይ ሲሰነጣጠቁ ለማሳየት እንጅ እንደገኘሁው ፓርቲ በጎ በጎውን ለመዘከር አይደለም፡፡ ይህ ቀድሞም የሚታወቅ ጉዳይ ቢሆንም እስከመቼ ‹‹የኢትዮጵያ›› ተብሎ አንድ ድርጅትን የማገልገሉ ነገር እንደ ትክክለኛ ነገር እየተቆጠረ እንደሚቆይ ግራ ነው፡፡

ትዝብት ሁለት፡- የገለልተኛት ተዝካር

ሕወሓት ጉባኤውን ሲያካሂድ በተግባርም ባይሆን ለስሙ ገለልተኛ ነው ተብሎ በሕገ መንግሥት የሰፈረው የአገር መከላከያ ኢታማጆር ሹም የሕወሓትን ኮፍያ አድርገው ትክክለኛ ነገር እንደሠራ ሰው በገሃድ ከጓዶቻቸው ተርታ መገኘታቸው ሕወሓት ከሕግ እና ሕጋዊነት ይልቅ ምን ያህል በወታደራዊ ጉልበቱ ወደ መተማመኑ ጭልጥ ብሎ እንደሄደ ማሳያ ነው፡፡ ነገሩን አቶ በረከት በ‹‹የሁለት ምርጫዎች ወግ›› መጽሐፋቸው ወታደሩ በአንድ ወቅት የሕወሓት አንድ አካል እንደነበረና አሁንም ነገሩ ሲከፋ ወደማን ሊሆን እንደሚችል መረሳት የለበትም ሲሉ የወታደሩን ወገንተኛነት ከሕዝብ ይልቅ ለእናት ድርጅቱ ሕወሓት እንደሆነ በጻፉት ማስፈራሪያ አዘል ማስገንዘቢያ ቀደም ብሎ የተገለጠ ቢሆነም ሰውየውን በገሃድ ስብሰባ ላይ አስቀምጦ በፈረደበት ኢቢሲ ማሳየት ግን ነገሩ የደረሰበትን የማናለብኝነት ዳርቻ ያስረዳል፡፡ የሚብሰው ደግሞ በተመሳሳይ ስለገልተኝነቱ በሕገ መንግሥት የተጻፈለት የመረጃና ደህንነት ተቋም ቁንጮ የሆኑትን ሰው ከፓርቲ ሥራ አስፈጻሚዎች ተርታ መጠቀሳቸው ነው፡፡

ትዝብት ሦስት፡- መተካካት ወዴት ወዴት!

ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አብዝተው በሥልጣን ላይ መወዘታቸውን በተመለከተ ውትወታ ሲበዛባቸው እንደማርያም መንገድ ይጠቀሙት የነበረው መተካካት የሚለውን ፈሊጥ ነበር፡፡ ሰውየው የመተካካቱን ፈለግ ሲናገሩ በሦስት ዙር ተከናውኖ የሦስተኛው ዙር ራሳቸውን አቶ መለስንም ከአመራር ገበታ እንደሚያነሳ ነበር ይገልጹ የነበረው፡፡ አቶ መለስ ይህን ሲሉ በሥልጣን ላይ ከሃያ ዓመት በላይ ኖረዋልና ‹‹ከሌሎች የአፍሪካ አምባገነኖች ምን ለየዎት?›› ከሚለው የምዕራባውያን ጋዜጠኞች ጥያቄ በመተካካት ሰበብ ፋታ ለማግኘት ነው፡፡ በስመ መተካካት ሦስተኛው የመተካካት ዙር እስኪደርስ ያለው ዘመንም ቀላል አይደለምና አጥብቀው ከሚወዱት ሥልጣን ላለመውረድ የመተካካትን ስም መደጋገሙ ጥሩ ሰበብ ነበር- ሞት ቀደመ እንጅ፡፡

የመተካካት ነገር ለአቶ መለስ ሌላም ጥቅም ነበረው፡፡ በትጥቅ ትግሉ ዘመን በጦር ሜዳ ውሎ ከአቶ መለስ ከራሳቸው ላቅ ያለ ጀብዱ የነበራቸው ታጋዮች እንደ ድል አጥቢያ አርበኞቹ ለአቶ መለስ መንበር ጎንበስ ቀና ብለው እንደሚፈለገው አቤት ወዴት ላይሉ ይችላሉ በሚል እነሱን ‹‹አረጋዊያን ናችሁና በቃችሁ›› ለማለት መተካካትን እንደ ስትራቴጅ መጠቀሙ ለአቶ መለስ ፍፁም ጠቅላይነት ፍላጎት ወሳኝ መንገድ ነበርና ሌት ተቀን ያቀነቅኑት ነበር፡፡ ማቀንቀን ብቻ ሳይሆን ብዙዎቹን ከሥልጣን ገበታ አስወግደውበታል፡፡ የተወገዱት ባለሥልጣናትም በወቅቱ መተካካቱን አምነውበት፣ ነገሩ ድርጅታቸው በአዳዲስ ጉልበት እየተመራ ራሱን እንደንስር እንዲያድስ የሚያግዝ፣ ከአቶ መለስ ብሩህ አዕምሮ የፈለቀ ድንቅ ነገር እንደሆነ፣ እነሱም ደስ እያላቸው ወደውና ፈቅደው ዱላቸውን ለተተኪ እንደሚያስረክቡ ያወሩ ነበር፡፡ ይህ የሆነው ታዲያ ተፈሪው አቶ መለስ ከነብርቱ ክንዳቸው በአፀደ ሥጋ በነበሩበት ወቅት ነው፡፡ አሁን አቶ መለስ አፈር ከገቡ ሦስት ዓመት ከሆናቸው በኋላ ግን ሌላ ዘፈን መጣ፡፡ እውነትም መንገድም ተደርጎ ሲወራለት የነበረው የመተካካት ጉዳይ እንዳልነበር ሆነ፡፡ ለአዲስ ተተኪ ኃይል ማስረከብ ቀርቶ አቶ መለስ በ1993ቱ የሕወሓት ‹‹ሕንፍሽፍሽ›› ከሥልጣን መዝገብ የሰረዟቸው ታጋዮች ሳይቀሩ ነፍስ ዘርተው ይንቀሳቀሱ ዘንድ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የመሆን ዘመን መጣላቸው፡፡

ይህ ብዙ የተባለለትን የመተካካት ጉዳይ ከአቶ መለስ ጋር አፈር ማስገባት የሚያሳየው ብዙ ነገር አለ፡፡ በጉልህ የሚያሳየው የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት በተለይ በትጥቅ ትግል እድሜያቸውን ያጋመሱት ታጋዮች እስከ ሽበት ሽምግልናቸውም ቢሆን ከሥልጣን መዐድ መለየት እንደሚያስቸግራቸው ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የትናንቶቹ ብረት አንጋቾች እነሱ የሚያወሩትን ዴሞክራሲያዊነት ሳይሆን የሚፈጽሙትን የአንድ ድርጅት የበላይነት በማስቀጠሉ ረገድ ከነሱ በኋላ የመጣውን ትውልድ ክንድ ብርታት አይተማመኑበትም፡፡ ይህችን ነገር አቶ ደመቀ መኮንን ለአማራ ክልል ቴሌቪዥን በሰጡት ቃለ ምልልስ ‹‹አዲሱ ትውልድ በሚፈለገው መጠን የመልካም አስተዳደርንና የዴሞክራሲያዊነት መርሆዎችን ከነባሩ አመራር አልወሰደም፤ ስለዚህም ነባሩ አመራር ትንሽ እንዲቆይ አስፈልጓል›› ሲሉ ገልጸውታል፡፡ አባባሉ የአገራችን ፖለቲካ ለሚገባው ሰው አቶ ደመቀ በቀጥታ ካሉት የተለየ ትርጉም አለው፡፡ ትርጉሙም ‹‹አዲሱ ትውልድ የነባሮችን ያህል የድርጅቱን ዘለዓለማዊነት ለማስቀጠል የሚቀረው ነገር አለ›› ለማለት እንጅ እውነት የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ነገር እነ አቶ ደመቀን አስጨንቆ አይደለም፡፡ ከዚህ በተቃራኒው አስቦ አቶ ደመቀ ያሉትን እንዳለ የሚያምን አንባቢ ካለ ነባሮቹ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት የትኛውን ዴሞክራሲያዊ ማንነታቸውን ነው ተተኪው አመራር መቀበል ያቃተው ብሎ ሊጠይቅ ግድ ነው፡፡

ሌላው የመተካካቱ ክሽፈት የሚያስገነዝበው ጉዳይ ኢሕአዴግ ትናንት ለተናገረው ነገር ተግባራዊነት እምብዛም ግድ የሌለው ድርጅት መሆኑን ብቻ ሳይሆን ቃል ያለማክበሩ የፖለቲካ ሚዛኑን ሊያቀለው የሚችል መሆኑን እንደማይገነዘብ፤ ቢገነዘብም እንደማያሳስበው ያስረዳል፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ ፓርቲው ከዚህ ባህሪው የተነሳ በአገሪቱ ሕዝብ ዘንድ ሊኖረው የሚችው ምስል ለወደፊት የመመረጥ ዕድሉን ሊያበላሽ ቢችል እንኳን ግድ እንደማይሰጠው አመላካች ነው፡፡ ይህ ሁሉ ሲጠቃለል በሕዝብ ይሁንታ ወደ ሥልጣን የመምጣቱ ጉዳይ ቁልፉ ያለው በእጁ ስለሆነ ለኢሕአዴግ የሕዝብ ስሜት እንደማያስጨንቀው ያረጋግጣል፡፡

የመለስ አምባገነንነት ፀሐይ ሲሞቀው ከመለስ ሞት በፊት በመተካካት ከድርጅቱ ተወግደዋል የተባሉት የሕወሓት ባለሥልጣናት በዘንድሮው የሕወሓት ጉባኤ ያለ ድምጽ እንዲሳተፉ ተጋብዘው ነበር፡፡ በስብሰባው ጅማሬ አንድ አባል ተነስተው ሰዎቹ ከድርጅቱ የወጡት ተገፍተው መሆኑን ጠቅሰው አሁን የመምረጥና የመመረጥ መብታቸው እንዲመለስ ሲጠይቁ የሐሳባቸው ተቀባይነት ማግኘት በጭጨባ ተገልፆ የጠየቁት እንደተደረገ ውስጥ አወቁ ሪፖርተር ጋዜጣ በወቅቱ ዘግቦ ነበር፡፡ ውሳኔው መተካካት የሚለውን የአቶ መለስ ዘይቤ ገደል የከተተ ብቻ ሳይሆን ሰውየው በሕይወት ዘመናቸው ደርሰውበት የነበረውን የአምባገነንነት ጠርዝ ያመላከተ ነው፡፡ ተመላሾቹ የሕወሓት ባለሥልጣናት ከትጥቅ ትግሉ ዘመን ጀምሮ የነበሩ መሆናቸው እንኳን የአቶ መለስን ቀጭን ትዕዛዝ ለመገዳደር አላስሞከራቸውም፤ እንደውም ‹‹ዱላ የምናቀብለው ደስ እያለን ነው›› ዓይነት ንግግር ይናገሩ ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ በተቃራኒው ‹‹የወጣነው ተገፍተን እንጅ የሥልጣንን መዓዛ አልጠገብንም›› እንደማለት እያሉ ነው፡፡ ይህ ማለት ገፊው የአቶ መለስ እጅ እጅግ ጠንካራ በመሆኑ ያልወደዱትን እንደወደዱ እንዲሆኑ እስከማስገደድ የሚደርስ፤ የባልደረባ ሳይሆን የጌታ እጅ ነበር ማለት ነው፡፡ ነገሩ የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲ በአቶ መለስ እጅ ተደፍጥጦ የኖረ መሆኑን አጋልጧል፡፡ ነገሩ ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር በሞቱ ሰሞን የግራ-ቀኝ ሐሳብ አዳማጭ፣ የተለያዩ ሐሳቦች አስታራቂ፣ ለውይይት ዝግጁ እንደነበሩ በአቶ አባይ ፀሐዬ አንደበት ከተነገረው ጎላ ብሎ የሚሰማ የአምባገነንነታቸው ምስክር ነው፡፡ በአንጻሩ ተገፍተን ወጣን ባዮቹም የማያምኑበትን ነገር እንዲያደርጉ የሚያስገድደውን የአቶ መለስን ጌትነት ለመገዳደር የተሳናቸው ጭምቶች እንደ ነበሩ አጋላጭ ነው፡፡ ሰዎቹ ‹‹ተራሮችን አንቀጥቅጠን አድባር አውጋሩን አስፈርጥጠን ለዴሞክራሲ የተዋጋን አርበኞች ነን›› የሚሉ መሆናቸው ደግሞ ነገሩን ይበልጥ ግራ ያደርገዋል፡፡


# መንቶች የዕጽዋት (የባህል) ማምረቻና መሸጫ

# MENTOCHE HERBAL MEDICINE PRODUCTION CENTER

ይህ የእጽዋት መድኃኒት ማዕከል ሲወርድ ሲዋረድ የነበረዉን የአባቶች የባህል /እጽዋት/ መድሀኒት ህክምና በማሳደግ ፍቱንነታቸዉ ተረጋግጦ በከፊል በሳይንስና ቴክኖሎጅ በማስመዝገብና ከኢንቨስትመንት ፈቃድ በመዉሰድ በማምረት ላይ ይገኛል። ለዉስጥ ችግር በሚወሰድ፣ በቆዳ ላይ ለሚወጣ በመቀባት ሲሆን ከኬሚካልም ሆነ ከባእድ ነገሮች ነጻ የሆነ ነዉ። ከሚመረቱት ምርቶች በከፊል

## በሚወሰድ

. ለኪንታሮት ፌስቱላ መድሀኒት በደም ዉስጥ ያለን አጥቦ የሚያወጣ ሲሆን ድርቀት፣ ወገብ ችግር፣ ጋዝና ወሲብ ችግርን ያድናል።

. ለነቀርሳ (ካንሰር) በሽታ ከደም ውስጥ አጥቦ የሚያወጣ በጭንቅላት፣ በአንገት፣ በጡትም ሆነ በአንጀት ላይ ያለዉን ያድናል።

.የደም ግፊት (ብዛት) እስከ መጨረሻዉ የሚያድን።

የኮሌስትሮል፣ የስብና የፕሮቲን ክምችትን ያቀልጣል፤ ስለሆንም ኮሌስትሮል ያጠፋል።

.ለነርቭ፣ ለሪህ፣ ለደም መወፈር (መርጋት) ለዲስክ መንሸራተት ያድናል።

.ለጉበት ሄፓታይተስ ሦስቱንም አይነት የጉበት በሽታ ያድናል።

. ለአእምሮ ጭንቀት ለሚጥል በሽታና ለሚያፈዘዉ ያድናል።

. ለቆዳ በሽታ አለርጅክም ሆነ ፈንገስ ሶራይስስ ጭምር ያድናል።

. ኤድስን የሚያባብሱ ተዛማጅ በሽታዎችን በማከም የድካም ስሜትን፣ መክሳትንና የምግብ ፍላጎት መቀነስን እንዲጨምር ያደርጋል።

. በሆድ ዉስጥ ላለ በሽታ አሜባ፣ ታይፎይድ፣ ጃርዲያ፣ አስካሪስና ዉሃ ወለድ በሽታዎችን ያድናል።

## የሚቀባና በፊንጣጣ የሚገባ መድኃኒት

. ለኪንታሮት (ፌስቱላ) በሚቀባ ምንም አይነት ህመም የሌለዉ ሲሆን ሥራም የማያስፈታ ነዉ። ለቆየ የአባላዘር ለዉስጥ ኪንታሮት በፊንጠጣ የሚገባ የዉስጥን የፈንገስ ክምችት የሚያወጣ ምንም አይነት የህመም ስሜት የሌለዉ ነዉ።

. ለቆዳ በሽታ ሁሉንም አይነት ያድናል

. ያለ እድሜ ለሚመጣ የወሲብ (የብልት መፍጠን) ችግር በመቀባት የሚያድን አብዛኛዉ ሕዝብ የኪንታሮት በሽታ በተመጣጣኝ ዋጋ እንሸጣለን።

በተጨማሪም በመገናኛ ውልና ማስረጃ ፊት ለፊት ገነት ኮሜርሻል ሴንተር 2ኛ ፎቅ የመድኃኒት መሸጫና የመርጃ ማእከል መክፈታችን ስናበስርዎ በደስታ ነዉ።

አድራሻ፡ አዲስ አበባ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ሃና ማርያም ከጤና ጣቢያዉ አለፍ ብሎ

0911 665321/ 0913 316790 / 0912 660886 / 011 4710024

ቁጥር 2፡ ሰሜን ሸዋ መሀል ሜዳ ወርልድ ቪዥን ፊት ለፊት

**BREAK THROUGH**
**ADVERTISING CONCEPTS**



- . Graphicd design
- . Printing
- . Communication
- . Advertising
- . poster
- . Flayers
- . Magazine and more

# NEBIYOU ADVERTISING

Tel; 0911 18 09 33
nebiyou1st@gmail.com
nebiyou1st@yahoo.com



## ምርጥ የፖለቲካ መፅሐፍ
# በገበያ ላይ

